# በእግዚአብሔር የተመረጠ
# የማምለኪያ ስፍራ

ለጸሎት አንገታችንን ዝቅ እንዳደረግን ለአፍታ ቆመን እንቆይ። አሁንም፡ አንገታችንን ዝቅ እንዳደርግን፡ ልባችንም፡ ዝቅ እንዳለ እምናለሁ፡ ዛሬ በተለየ መልኩ፡ በጸሎት መታሰብ የምትፈልጉ ሰንቶች ናችሁ? እጆቻችሁን ከፍ አድርጋችሁ፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ የምፈልገውን ዛሬ ማታ ስጠኝ፡" ብቻ በሉት። ጌታ ይባርካችሁ።

2 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ በትህትና ወደዚህ ታላቅ የጸጋ ዙፋን አሁን ስንቀርብ፡ በእምነትም፡ ከፍ ወዳለው፡ እግዚአብሔር፡ መላእክት፡ እና ኪሩቤሎች፡ እና የሰማይ ሠራዊት ሁሉ በአንድነት ወዳሉበት እንወጣለን። የሰማይ አባት ሳያውቅ በምድር ላይ የምትወድቅ ድንቢጥ እንኳን እንደማትኖር ተናግሯልና። ታዲያ እዚህ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አንገታቸውን ደፍተው በልዩ ልመና ሲጠሩት፡ ከዚያ ይልቅ እንዴት አብልጦ ያውቅ ይሆን። አባት ሆይ፡ የተቸገርን ህዝቦች ነንና፡ በችግር ላይ ባለ ህዝብ ላይ ዛሬ ተመልከት።

3 እግዚአብሔር ሆይ፡ በዚህ ተሰብሰበናልና፡ እጸልያለሁ እንዲሁም ጸሎትን በሚመልስ በሕያው አምላክ ላይ ያለንን እምነት ለአንተ እንገልጻለን፥ ልባቸው እና ጆሮዎቻቸው ካልተገረዙት፡ ከዓለም መካከል ወጥተን፡ የተለየ ሕይወት ለመኖር እና፡ በአንተ ያለንን እምነት ለመመሰከር መጥተናል። ዛሬ ምሽትም እጆቻችንን ከፍ አድርገን፡ "ችግረኞች ነን፡" እንልሃለን። አምላክ ሆይ፡ የሁሉንም ልመና መልስ።

4 ስለዚህም፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ምሽት በቃሉ ላይ እንድትጎበኘን እንለምናለን። በዚህ ዘመን እንዴት እንደምንኖር እናውቅ ዘንድ፡ ለመታረም፡ ምን መጠበቅ እንዳለብን፡ ምን ማድረግ እንዳለብን፡ ለማስተዋል ወደዚህ መጥተናል። ነቢያት እንደተነበዩት በምልክቶች ሁሉ፡ የጌታ መምጣት እየቀረበ መሆኑን፡ አውቀናልና። ጌታ ሆይ፡ ፍጹም መዳን ለልጆችህ ወደሚሰጥበት ጊዜ፡ ተቃርበናል። እግዚአብሔር ሆይ፡ አባት ሆይ፡ ሁላችንም፡ በዚያ መገኘት፡ ይሁንልን። የሚጎድል አይኑር። ጌታ ሆይ፡ እዚህ የመኖራችን አላማ ይህ ነው። እንወድሃለን፡ እናም ለዚያ ሰዓት ለመዘጋጀት እየሞከርን ነው።

5 ዛሬ ማታም፡ ትናገረን ዘንድ፡ ደግመን እንጠይቅሃለን። የታመሙትንም ፈውስ። በሕንፃው ውስጥ ያሉት ሕሙማንና ደካሞች ሁሉ፡ ጌታ ሆይ፡ እንድትፈውሳቸው እንጸልያለን፥ በተለይ ደግሞ በመንፍሳዊ ችግር ያሉትን። የጠፉችውን ነፍስ ሁሉ እንድታድን እንጸልያለን። እያንዳንዱን አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ሙላ። በሚያምኑ ልጆችህም ጥንካሬን እና ኃይላቸውን አድስ። እነዚህን ነገሮች አድርግልን፡ አባት ሆይ። ጠይቁ ስላልከን፡ አብዝተን ጠየቅንህ፡ ደስታችን ይፈጸም ዘንድ "አብዝታችሁ ጠይቁ፡ ብዙዎቹን፡ ታላልቅ ነገሮች ለምኑ፡" አልከን። እኛም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

6 በዚህ ምሽት፡ እንደገና ወደ መድረክ፡ እዚህ በዚህ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በመገኘቴ፡ ወንጌልን ለመስማት በተሰበሰቡት ጥሩ ሰዎች ፊት ስለመጣው እንደ ታላቅ ክብር እቆጥረዋለሁ። ያወቅኩትን ያህል እውነት እንድነግራችሁ እንዲረዳኝ የእግዚአብሄርን ምህረት እጠይቃለሁ። የአንበሳን አፍ መዝጋት እንደሚችል ሁሉ፡ አሁንም የሰውን አፍ መዝጋት ይችላል። እናም ከራሱ ፈቃድ ጋር የሚቃረን ማንኛውንም ነገር ለመናገር ብሞክር፡ እንዳልናገር አፌን እንዲዘጋው፡ ልባዊ ጸሎቴ ነው። በእውነት፡ እኔ ራሴም፡ ገነት መግባት፡ እፈልጋለሁና፥ አንድን ነገር በሐሰት እንዳደረገ ሰው፡ እኔም፡ በዚያ ላልገባ፡ እችላለሁና፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ሐሰተኛ መሪ መባል አልፈልግም። ያን ካደረግኩ ግን፡ ከዚያ የተሻለ ስለማላውቅ ነው። ጌታ ይባርካችሁ።

7 እንግዲህ፡ ነገ ጥዋት፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፡ ስለ **ጋብቻ እና ፍቺ፡** ለመናገር አስቤአለሁ። እናንተም ማስታወሻችሁ እና ብዕራችሁን፡ ይዛችሁ እንደምትመጡ እናምናለን። በጣም ረጅም ጊዜ አንወስድም፡ አንድ ነገር ግን እፈልጋለሁ… በመጀመሪያም፡ ወደዚህ ኢንዲያና፡ የተመለስኩበት አላማ ያ ነበር፡ ያንን ቃል ገብቼላችኋለሁና። እና ነገ ጠዋት፡ እሞክራለሁ። ነገ ጠዋት ካልቻልኩ፡ ነገ ማታ አደርገዋለሁ። ነገ ጠዋት ግን እሞክራለሁ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ለመናገር፡ ስለ ሁለቱ ሃሳባዊ ትምህርቶች እናገራለሁ። በእውነት እና በብርሃን እንድንመላለስ፡ እግዚአብሔር እውነት የሆነውን እንድናውቅ፡ እውነት የሆነውን ለማወቅ ብቻ ይርዳን። እኛ…

8 እንደምታውቁት፡ አንድ ጥቁር ወዳጅ ነበርኝ። እንዲህ አለኝ፡ "ወንድም ቢሊ፡" አለኝ፡ "በዚያ በዳርቻዋ ላይ ምንም አይነት ችግር አ—አልፈልግም፡" አለኝ። እንዲህ አለ፡ "እኔ ቲኬቴን በእጄ መያዝ እፈልጋለሁ። መለከቱ ሲነፋም፡ ምንም ችግር እንዲኖርብኝ አልፈልግም። ከረጅም ጊዜ በፊት፡ የሆነ ችግር ካለብኝ፡ አሁን ላስተካክለው ብዬ፡ ጌታን ጠይቄዋለሁ፡" "ምክንያቱም በዚያ ጠዋት መርከቧ ወደ ሌላኛው ዳርቻ ስትጎተት ጨለማና ጭጋግ ይሆናልና፡" አለኝ። "ምንም አይነት ጣልቃ ገብነት አልፈልግም። አሁን ሁሉንም ነገር ራሴ ማስተካከል እፈልጋለሁ፡" አለኝ። እኛ እዚህ ያለነው ለዚያ ነው፡ ሁሉንም ጣልቃገብነቶች ለማስተካከል ነው፡ ያቺ ሰዓት በደረሰች ጊዜ ተሳፍረን መሄድ እንችላለንና።

9 አሁን፡ ነገ ሁለት አገልግሎቶች ስለሚኖሩን፡ ዛሬ ምሽት ብዙ አላቆያችሁም። ከዚያ በኋላ፡ በሌላ ሰፍራ፡ ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት ለማድረግ፡ ወዲያው እሄዳለሁ።

10 አሁን፡ ግን፡ በዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ። ከዘዳግም ከ16ኛው ምዕራፍ፡ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ቁጥሮች ማንበብ እፈልጋለሁ፡ ዘዳግም 16፡1 እስከ 3 ድረስ።

> **በአቢብ ወር አምላክህ እግዚአብሔር… በሌሊት ከግብፅ ስላወጣህ፡ ፋሲካ አድርግበት፥ …** (በአራተኛው) **በአቢብ ወር አምላክህ እግዚአብሔር በሌሊት—ከግብፅ ስላወጣህ የአቢብን ወር ጠብቅ።**
>
> **አምላክህ እግዚአብሔር በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ በመረጠው** ስፍራ፡**ለአምላክህ ከላም** መንጋ **ፋሲካ ሠዋ፡**

**የአምላክህንም የእግዚአብሔርን** በመረጠው **ስፍራ።**

11 አሁን፡ የዛሬ ምሽት ርዕሴ፥ **በእግዚአብሔር የተመረጠ የማምለኪያ ስፍራ** ነው።

ልብ ብላችሁ ከሆነ፡ አ-ቢ-ብ... -ብ በመባል የሚታወቀው ወር፡ "ሚያዝያ፡" ማለት ነው። የወጡበት ወር ሚያዝያ ነው።

እና አሁን የሚገርመው ነገር እኛ ዛሬ ማታ፡ እግዚአብሔርን የምናመልክ ስንሆን፡ በዚህ በምንኖርበት ዘመን፡ የሰዎችን በጣም ብዙ የተለያዩ አሳቦች እንዳሉ እናያለን። ስለዚህ የነገሮች የተለያዩ አሳቦች እስካሉ ድረስ፡ የተለያዩ ጥያቄዎች ደግሞ ይኖራሉ፥ ስለዚህ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች ሁሉ አንድ እውነተኛ መልስ ሊኖር ይገባል።

"**ይህ** ምንድነው፡" የሚል ጥያቄ ብጠይቅ?

"ይሄ'ማ፡" "ጠረጴዛ ነው፡" ይሉኛል።

"ለምንድን ነው? " እያችሁ?

12 እንግዲህ፡ አንድ ሰው እንዲህ ሊል ይችላል፡ "ይህ ጠረጴዛ አይደለም። ቦርድ ነው።" አዎን፡ ቦርድ ነው፡ ግን ደግሞ ጠረጴዛም ነው። እያችሁ፡ እውነተኛ መልስ ሊኖረው ይገባል።

ስለዚህ ስለማንኛውም ነገር ጥያቄ ብጠይቅ፡ እውነተኛ መልስ ሊኖር ይገባል። ወደ እሱ ቅርብ የሆነ መልስ ሊኖር ይችላል፡ ይሁን እንጂ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ግን እውነተኛና፡ ቀጥተኛ መልስ መኖር አለበት። ስለዚህ፡ በህይወታችን ውስጥ ለሚነሳው እያንዳንዱ ጥያቄ፡ ትክክለኛ፡ እውነተኛ፡ መልስ መኖር አለበት።

13 እና አሁንም፡ ዛሬ ላይ፡ ሲባል—እንደምንሰማው፡ ዛሬ በዓለም ላይ ያሉ ብዙ ወገኖቻችን...

ሚስዮናዊ እንደመሆኔ፡ በባህር እና በአለም ዙሪያ ብዙ ጉዞዎችን አድርጌአለሁ፡ ከተለያዩ ሃይማኖቶች ጋር ግንኙነት አለኝ፡ እንደ ቡድሃ፡ እና መሃመዳውያን፡ እና ሲክሶች፡ እና ጄይን፡ እና-ሌሎችም፡ የአለም ሀይማኖቶች ተገናኝቼ አውቃለሁ። ከዚያም እዚህ በራሳችን ዩናይትድ ስቴትስ፡ እና ሌሎች የውጭ ሀገራትም፡ እንደ ሐይማኖት ተቋሞቻችን የመሳሰሉ አብያተ ክርስቲያናት ጋር፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተገናኝቻለሁ፡ ከጥንታዊው የሮማ ካቶሊክ ጀምሮ፡ ከዚያም ወደ ግሪክ፡ እና የመሳሰሉት፡ ከ—ከተለያዩ ጎራዎች ጋር፡ እና ከዚያም... ሁሉም የቤተ እምነት ዘመናት፡ ዘጠኝ መቶ እና የሆነ የተለየ የፕሮቴስታንት ቤተ እምነቶች።

አሁን፡ እያንዳንዳቸው፡ በእርግጥ፡ ሃሳባቸውን ማየት ትችላላችሁ፡ እና እነሱን መውቀስ አልችልም። እያንዳንዳቸው እውነት ይዘናል፡ እውነት አለን ይላሉ። የእነዚያም አብያተ ክርስቲያናት የሆኑ ሰዎች እንዲያ ብለው ማመን ይጠበቅባቸዋል፡ ምክንያቱም መዳረሻቸውን፡ ዘለአለማዊ መዳረሻቸውን፡ በዚያ ቤተ ክርቲያናቸው አስተምህሮ ላይ አስምረው—ወግተዋል። እና ዘጠኝ መቶ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች እስኪፈጠሩ ድረስ፡ አንዱ ከሌላው፡ እጅግ የተለያዩ ናቸው።

ስለዚህ፡ ዘጠኝ መቶ እና ከዚያ በላይ ጥያቄዎች በመሆናቸው፡ ለሁሉም አንድ ትክክለኛ መልስ ሊኖር ይገባል። እኛም ዛሬ ማታ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ፡ እና ሁላችንም የምንወደውን ጌታችንን ኢየሱስን ለመገናኘት፡ እየሞከርን ያለን በመሆናችን፡ መልሱን ለማግኘት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መፈተሽ እፈልጋለሁ።

14 ስለዚህ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ ከሆነ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ሊኖረው ይገባል። ከአንድ የተለየ የሰዎች ቡድን፡ ወይም ከአንድ ሕብረት፡ ወይም ከአንድ አስተማሪ፡ ወይም ከአንድ የሐይማኖት ተቋም መምጣት የለበትም። በቀጥታ የእግዚአብሔር የመገናኛው፡ የአምልኮ ስፍራ ከሆነው፡ ከቃሉ ዘንድ መምጣት አለበት። በእውነትም፡ አምላክ ስለሆነ፡ እሱ የሚገኝበት፡ የመገናኛ ስፍራ አለው።

15 እንግዲህ፡ እዚህ በዘዳግም ውስጥ፡ መጀመሪያ ላይ፡ ሙሴ አስቀድሞ የነገራቸው ነገሮች፡ ቅዱስ ቃላትን እንደገና ሲያነብላቸው፡ በታላቅና በብርቱ ክንድ፡ ከግብፅ እንዴት እንዳወጣቸው፡ እና እንዴት እንዳጸናቸው አነበበላቸው።

ከግብጽ እስኪወጡ ድረስ “የእግዚአብሔር ህዝብ” በመባል ይታወቁ ነበር፡ ከዚያ በኋላ “የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን” ተባሉ። ምክንያቱ፡ ቸርች መሰብሰቢያ፡ ወይም፡ ስለ እውነት ከሆነ፡ **ቸርች** ማለት “የተጠሩ-ሰዎች፡” የተጠሩ ግለሰቦች ማለት ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ለመሆንም፡ ከግብጽ ወጡ።

16 አሁን ቤተ መቅደሱን ከመመሥረታቸው በፊት፡ እና ሌላው ሁሉ ከማድረጋቸው በፊት... እግዚአብሔር ተናገራቸው፡ “የማምለኪያዬን ስፍራ እመርጣለሁ፡ በዚያም ስሜንም እኖራለሁ።” እና እግዚአብሔር ከማንም ጋር የሚገናኝበት ቦታም፡ በራሱ በሚመርጠው ስፍራ ብቻ ላይ ነው። ስፍራውን ይመርጣል፡ በመረጠው ስፍራ ውስጥ፡ በዚያ ስሙን ያኖርበታል፡ እዚህ ያለው በ 2ኛው ቁጥር የሚነግረን፡ ሰዎች እንዲያመልኩት በመረጠው ቦታ ስሙን እንደሚያስቀምጥ ነው። ስለዚህ፡ የዚህ ነገር ዋናው ቁምነገር፡ ስፍራው የት መሆኑን መፈለግ አለብን ነው።

17 እኛ ግን ስለ ክርስትና ሐይማኖት እየተናገርን፡ ከዘጠኝ መቶ እና ከዚያ በላይ በሆኑ ልዩ ልዩ አሳቦች፡ የአረማውያን ሐይማኖታትን አልፈን ሄደናል። ቢሆንም፡ እኔ ለአረማውያን አዝንላቸዋለሁ፡ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ወደዚያ ሄጄ ባላነጋገርኳቸው ነበር። ይሁን እንጂ፡ እነርሱ ተሳስተዋል። ክርስትና ብቸኛው እውነተኛ ሐይማኖት ነው፡ ክርስትና ብቻ። ይህን የምለው ክርስቲያን በመሆኔ አይደለም፥ ሳይሆን፡ እውነት መሆኑን ስለማምን ነው። ብቸኛው ትክክለኛው ሃይማኖት ይህ ነው።

18 በየአራት ሰዓቱ ነጭ ፈረስ ወደሚቀየርበት መቃብሩ ሄጄ ነበር። በዚያም፡ መሐመድ፡ ታላቁ ካህን—ከክርስቶስ በኋላ የመጣ አለቃ፡ ነቢይ ነው ተብሎ ይገመታል፡ እና፡ እንደዚያ መሆኑም አልጠራጠርም፡ከመቃቢያን ወንድሞች በኋላ የመጣ ነበር። እና ያን ጊዜ... ሞተ። ዳግመኛ እንደሚነሣ እና ዓለምን ከቁጥጥር ስር እንደሚያውላት ተናግሮ ሞተ። በዚህ ሰዓት፡ በየአራታ ሰዓቱ ጠባቂዎች ይቀያየራሉ፡ መቃብሩ ላይም ሁሌ የሚቆም ነጭ ፈረስ ያስቀምጣሉ።

ዳግመኛ እንዲነሣና፡ ዓለምን እንዲያሸንፍ በመመኘት፡ ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል እየጠበቁት ይገኛሉ። ይሁን እንጂ እንደምታዩት...

19 እና ቡድሃን ደግሞ ተመልከቱ፥ ቡድሃ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የኖረ፡ ከሁለት ሺ-ሦስት መቶ ዓመታት በፊት የነበረ፡ የጃፓን—አምላክ ነው። እሱም እንደ ኮንፊሺየስ፡ እና እንደ ሌሎቹ፡ ፈላሰፋ ነበር።

እነዚያ ሁሉ፡ መ... .መሰራቾች፡ እና ሌሎች፡ ከነፍልሰፍናቸው ሞቱ፡ ተቀብረውም በመቃብራቸው ቀርተዋል።

በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰረተው፡ ክርስትና ግን፡ ባለ ባዶ መቃብር ነው። በምድር ላይ ቆሞ፡ በህይወት ሳለ እንዲህ ብሎ የተናገረ ብቸኛ ሰው ነው፡- "ነፍሴን ላኖራትም እንደገና ላነሣትም ስልጣን አለኝ።" እንዳለም አደረገ። ስለዚህ ዛሬ ህያው ነው።

ህያው መሆኑ እኛም እናውቃለን፡ ከእኛ ጋር ነውና በሥጋ ምልክትና ድንቆች አሳያችኋለሁ ብሎ ቃል የገባልንን ነገሮች፡ እያሳየን ራሱን ሰላረጋገጠልን ሕያው መሆኑን እናውቃለን። ስለዚህ፡ የእስራኤልን ልጆች በምድረ በዳ የእሳት ዓምድ እንዳሳለፋቸው፡ ዛሬም ከእኛ ጋር ነው፡ ፎቶውን ሳይቀር ተነስቷል፥ በዚህ ዘመን አደርገዋለሁ በማለት ቃል የገባልንን ድንቆች እና ምልክቶች እያደረገ ይገኛል፡ የገባውን ቃል ሁሉ በዚህ ዘመን ሲገለጥ አይተናልና። ስለዚህ፡ ሌላው የአረማውያን ዓለም ከጨዋታ ውጭ ነው። ክርስትና ብቻ ነው!

20 አሁን፡ እግዚአብሔር የት እንደሚገናኘን ዘጠኝ መቶ እና ከዚያ በላይ ጥያቄዎች ሰላሉ፡ "መገናኛው ከሜቶዲስት ጋር ነው፡ ወይም በባፕቲስት ውስጥ ይገናኘናል፡ **በዚህ** ይገናኘናል፡ **በዚያ፡** እና **በሌላም** ይገናኘናል።" አሁን፡ እያንዳንዱ ሰው በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ የራሱን መዳን መፈለግ ሰላለበት፡ እዚጋ አንድ ጥያቄ አለ።

ዛሬ ማታ ግን እግዚአብሔር፡ ከሰዎች ጋር የሚገናኝበት እና የሚያመልክበት፡ ትክክለኛው ቦታ ለመመርመር እና በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ። እና፡ ይህ ነው ከተባለም፡ እሱ የሚገናኝበት ብቸኛው ሰፍራ ያ ይሆናል።

21 አሁን፡ ይህ ጽሑፍ ከዘዳግም ውስጥ እንውሰድ። ይህም ባለ ሁለት ወይም ድርብ ትርጉም ያለው የግሪክ ቃል ነው፡ ወይም፡ "ሁለት ሕጎች፡" ማለት ነው። **ዘዳግም፡** የሚለው በግሪክ ቃል፡ "ሁለት የተለያዩ ህጎች" ማለት ነው።

ይህም እግዚአብሔር፡ ሁለት የተለያዩ ሕጎች ሰላሉት ነው። አንደኛው የሞት ሕግ ነው፡ ሌላኛው ደግሞ የሕይወት ሕግ ነው። እግዚአብሔር ሁለት ህጎች አሉት። እርሱን መከተል፡ እና ማገልገል እና ማምለክ ህይወት ነው፥ አለመቀበል ሞት ነው። በእግዚአብሔር ውስጥ ሁለት ሕጎች አሉ።

22 አሁን፡ ከእነዚያ ሕጎች ውስጥ አንዱ እውቅና-... በሲና ተራራ፡ በዓለም እውቅና ተሰጥቶታል። እግዚአብሔር ለሙሴና ለእስራኤል ሕጉን ሰጠ። ሕጉ ሊረዳቸው እንደሚችል ሳይሆን፡ ሕጉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ብቻ ያሳያል። እስከዚያ ጊዜ ድረሰ ግን፡ ሕግ እስኪመጣ ድረሰ ግን፡ ኃጢአት ምን እንደነበረ እንኳ አያውቁም። ቅጣት የሌለው ሕግ ሊኖር አይችልም። ቅጣት የሌለው ሕግ፡ ሕግ አይደለም። ስለዚህም፡ ምክንያት፡ "የሕግ መተላለፍ ኃጢአት

ነው፡ የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው።" ስለዚህም ምክንያት፡ እግዚአብሔር ሕግ እስከሚሰጣቸው ድረስ፡ እንደ ኃጢያት የሚቆጠርባቸው መተላለፍ አልነበረም።

በሰአት ከሃያ ማይል በላይ መንዳት እንደማትችል የሚገልጽ ህግ ከሌለ፡ በሰአት ከሃያ ማይል በላይ መንዳት ትችላለህ። አይቻልም የሚል ሕግ ካለ ግን፡ እንግዲያውስ ከበሰተጀርባው ቅጣት ያለው ሕግ መኖሩ ግድ ነው።

23 እንግዲህ፡ ሞት፡ የሞት ህግ፡ በሲና ተራራ ላይ የተሰጡት ትእዛዛት ናቸው፡ ይህም ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን ይነግራል። ስለዚህ፡ የእግዚአብሔርን ሕግ በመጣስ፡ ይሞታል። ይሁን እንጂ በሕግ ውስጥ መዳን የለም። ፖሊስ... ወደ እስር ቤት ብቻ ያወርዳችኋል እንጂ፥ እናንተን ከዚያ የማስወጣት ስልጣን የለውም።

ነገር ግን በቀራንዮ ተራራ ላይ፡ ሌላ ህግ ሰጠን፡ በዚያም የኃጢአት ዕዳ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ተቆጠረ፡ ዕዳውም በዚያ ተከፈለ። ስለዚህ ያለዚህ... ያለ ሕግ፡ "በጸጋው ድናችኋልና፡" በእግዚአብሔር ጸጋ፡ ስለ ማንነታችሁ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የመታወቅ ጸጋ።

24 አሁን እነዚህን ሁለት ሕጎች፡ ዘዳግም፡ ስለ ሁለት ሕግጋት ሲናገር እናያለን። ሁለት ህጎች ነበሩ። አንደኛው የሞት ሕግ ሲሆን፡ ሁለተኛው ደግሞ የሕይወት ሕግ ነበር።

25 ለሰዎች የተሰጡ ሁለት ቃል ኪዳኖችም ነበሩ። ስለእነሱም ጠዋት ላይ እንነጋገራለን።

አንደኛውም "**ይህን** ካደረጋችሁ እና **ያን** ካላደረጋችሁ፡" በሚል በቅደመ ሁኔታ ለአዳም የተሰጠ ነበር፡ ያ ህግ ግን ተሰብረዋል። አዳም፡ ማለቴ ሔዋን ያንን ነገር፡ በኤደን ገነት ሰበረችው።

ከዚያም እግዚአብሔር ሁለተኛውን ቃል ኪዳን አደረገ፡ ያንንም ለአብርሃም ሰጠው፡ እናም ያ ሕግ ምንም ቅድመ ሁኔታ አልነበረውም። "እናንተ በሰራችሁት ወይም በምትሰሩት አይደለም፥" "እኔ ራሴ ሰርቼዋለሁ፡" አላቸው። ጸጋ ማለት ያ ነው። የህይወትን ህግ ያ ነው። እግዚአብሔር ያንን ለአብርሃምና፡ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ፡ ማለትም ለአብርሃም ዘር ሁሉ አደረገ።

መጽሐፍ ቅዱስም "እስራኤል ሁሉ ይድናሉ፡" እንዳለ ነው፡ ይህ ማለት ግን አይሁዶች ማለት አይደለም። ጳውሎስም እንደተናገራቸው፡ "ከውስጥ እስራኤል ለሆኑት፡ ወይም ከውጭ እስራኤል ለነበሩት።" "ከውጭ፡" በቀደም ምሽት ላይ እንደተነጋገርን፡ እነሱ በግብረ ስጋ፡ የይስሐቅ ልጆች ነበሩ። የእግዚአብሔር ሕግ ግን፡ የአብርሃም ንጉሳዊ ዘር በሆነው በክርስቶስ ነበረ፡ ይህም፡ "እስራኤል ሁሉ በጸጋው ድነዋል።" ይኸውም፡ "በክርስቶስ ያለው ሁሉ ድኗል፡" ይህም፡ የእግዚአብሔር ሁለተኛ ቃል ኪዳን ነው። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ነገሮች ለክርስቶስ ጥላ ነበሩ።

26 አሁን በ2ኛው ቁጥር ላይ አስተውሉ። በዘዳግም 16፡ በ2ኛው ቁጥር ላይ፡ "እኔ በመረጥኩት ስፍራ አምልኮ አድርጉ" ይላል። አሁን እግዚአብሔርን አምልኩት፡ "በመረጥኩት ስፍራ፡" መሆን አለበት አላቸው፡ ሌላ ሰው የመረጠው፡ ሳይሆን፡ "እኔ የመረጥኩት።"

አሁን፡ እግዚአብሔር ስፍራን ከመረጠ፡ ስለ እሱ የተናገረውን ማወቅ ያስፈልገናል። እንዲሁም ስፍራው የት ነው? ላገኘው እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱ፡ በእውነት፡ እኔ እርሱን ማምለክ እፈልጋለሁ።

ዛሬ ምታ፡ ሁላችንም፡ እርሱን ለማምለክ እዚህ ተገኝተናል። እንደ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ካቶሊክ፣ የይሖዋ ምሥክር፣ የክርስቲያን ሳይንስ፣ እና ሁሉም፣ ዛሬ ማታ እዚህ ተገኝተናል፡ ነገር ግን ሁላችንም አንዳች ነገር እንፈልጋለን።

እውነትን ማወቅ እንፈልጋለን። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "እውነትን ታውቃላችሁ፡ እውነትም አርነት ያወጣችኋል።"

ምን እየሰራህ እንደሆነ የማታውቅ፡ ግለሰብ፡ እንዴት ማድረግ እንደሚገባህ እስክታውቅ ድረስ እንዴት ማድረግ እንዳለብህ አታውቅም፥ ማለቴ፡ እንዴት ማድረግ እንዳለብህ እስክታውቅ ድረስ ምን ማድረግ እንዳለብህ አታውቅም። እንዴት ማድረግ እንዳለብህ እና ምን ማድረግ እንዳለብህ ልታውቅ ይገባሃል።

27 ይህ የሚያሳየን እግዚአብሔር ለሚያመልኩት መሰብሰቢያ ቦታ፡ በአንድ የተወሰነ ስፍራ ላይ እንዳለው ነው። እግዚአብሔር ከሚያመልኩት ጋር፡ በዚያ ስፍራ ብቻ፡ ይገናኛል።

28 አሁን፡ በተጨማሪም፡ ሊያመልኩት በወሰነላቸ ስፍራ፡ በዚያ ስፍራ ውስጥ ስሜን አኖራለሁ አላቸው። አሁን ስፍራው የት እንዳለች፡ በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል፡ ፈልገን እናገኝ። በእርግጥም፡ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ለመገናኘት በመረጠው ስፍራ ከእነርሱ ጋር ለማምለክ ማለቴ፡ እርሱን ያመልኩት ዘንድ፡ ስሜን በዚህ አኖራለሁ ካለ... እንግዲያውስ በዘመናት ሁሉ ላይ ስለኖረች፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሆነ ስፍራ ላይ ትገኛለች።

29 ታላቁ የማይለወጥ አምላክም አይለዋወጥም። ሰው ይለዋወጣል። እግዚአብሔር በተናገረው ነገር ላይ ግን ህይወታችሁን በማንኛውም ጊዜ ማድረግ ትችላላችሁ፡ እውነት ስለሆነ። እውነት ነው። ምክንያቱም፡ ልተማመንበት የምችለው ብቸኛው ነገር፡ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ምክንያቱም፡ የሰው ቃል ይወድቃል፡ እግዚአብሔር ግን ሉአላዊ ነው።

በዚህ አመት ካለፈው አመት በበለጠ ማወቅ አለብኝ። እናንተም፡ በየቀኑ፡ ማወቅ አለባችሁ። እኛ ውሱንነት ስላለብን፡ እውቀትን እንገበያለን።

እግዚአብሔር ግን ወሰን የለውም። እሱ ፍጻሜ የለውም። እና፡ ፍጻሜ የሌለው በመሆኑ፡ እውቀትን መጨመር አይችልም። ሲጀመር፡ እርሱ ፍጹም ነው። እያንዳንዷ ውሳኔው ሁሌ ትክክል ናት።

30 እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ባደረገበት መንገድ፡ ለዘላለም እንደዚያ መቀጠል አለበት፡ ካልሆነ ግን መጀመሪያ ሲሰራ ስህተት ነበረው ማለት ነው። እግዚአብሔር እርሱን በተቀበለበት መሠረት፡ አንድ ሰው ለመዳን ወደ እርሱ ቢመጣ፡ ሁሉጊዜ በተመሳሳይ መሠረት መቀበል አለበት። ትክክል ነው። አንድ ሰው መለኮታዊ ፈውስ ፈልጎ ወደ እግዚአብሔር ቢመጣ፡ እግዚአብሔርም በተወሰኑ መስፈርቶች መሠረት ቢቀበለው፡ ከሱ ቀጥሎ ለሚመጣው ሰው፡ በተመሳሳይ መስፈርት ሊቀበለው ይገባል፡ ካልሆነ ግን የመጀመሪያ ሰው በተቀበለ ጊዜ ስሕተት ፈጥሯል። እግዚአብሔር

ከሰው ጋር የሚገናኝበትን መሰፈርት አበጀ። ምን እንደሚያደርግ፡ እና እንዴት እንደሚያደርገው መሰፈርት አበጀ፡ ይህም በኤደን ገነት በነበረው የበግ መሥዋዕት ደም ነው። እግዚአብሔርም፡ መቼም ቢሆን፡ ይሄን አልለወጠውም።

31 ሰውን እንዴት እንደሚያድን ወሰነ። እኛ ደግሞ ዛሬ ሰውን ወደ እሱ ለማስተማር እንሞክራለን፥ ትምህርት ለመስጠት እንሞክራለን፡ ስልጠና ለመስጠት እንሞክራለን፡ ተቋም ለማድረግ እንሞክራለን፡ እነዚያን ነገሮች ሁሉ ለማድረግ እንጋጋጣለን፥ እናስገባቸዋለን፡ እንወዘውዛቸዋለን፡ እናጠምቃቸዋለን፡ አለ የተባለ ነገር ሁሉ እናደርጋለን፡ በደብዳቤ ሳይቀር እናስገባቸዋለን። እግዚአብሔር ግን፡ በፈሰሰው በበጉ ደም ስር ያለውን ሰው ለመገናኘት፡ አሁንም ያው ነው። ከመጀመሪያ ጀምሮ የእግዚአብሄር መንገድ በደም ነበረ፡ ዛሬ የእግዚአብሔር መንገድ በደም በኩል ነው። ንስሐ መግባት እና እነዚህን ሁሉ ማድረግ ጥሩ ነው፡ መዳን የሚገኘው ግን በደም ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የመረጠው ብቸኛው መንገድ ደም ነው፡ ሊለውጠውም አይችልም።

32 በኢዮብም ዘንድም ተመሳሳይ ነገር ነበረ። እግዚአብሔር አቅርብልኝ ብሎ ያዘዘው—መስዋዕትን ስላቀረበ፡ ጻድቅ መሆኑን ያውቅ ነበር።

33 አሁን፡ ይህ ቦታ ምን እንደሆነ፡ እና ሰሙን ያስቀመጠበትን ስፍራ ለማየት አሁን እንፈልገው። ሰሙን የት እንዳኖረው ማወቅ አለብን። ከዚያ በኋላ፡ የእግዚአብሔር ሰም ማን እንደሆነና የት እንዳስቀመጠው ካወቅን፡ ይሄን ከተረዳን የማምለኪያው ስፍራ ወዲያ አግኝተነዋል ማለት ነው።

እነዚህ ሁሉ ነገሮች፡ በእርግጥ፡ ለሚመጡት ነገሮች ጥላ ነበሩ። ሕጉ ሁሉ ለሚመጡት ነገሮች ጥላ ነበር።

34 ጨረቃ፡ የፀሐይ ጥላ እንደሆነች ሁሉ። ፀሐይ በሌለበት ታገለግላለች፡ ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር ልጅ S-o-n በሌለበት እንደምታገለግል። ልጅ በለሌ ጊዜ፡ ትንሿ ብርሃን፡ ይህም ቤተ ክርስቲያን፡ ማለት አማኞቹ፡ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ ልጅ በማይኖር ወቅት ብርሃን ይሰጣሉ። ፀሐይ ስትወጣ ግን፡ ጨረቃን አታዩአትም፡ ምክንያቱም ትወርዳለች። ከዚያ በኋላ ብርሃኗ አያስፈልግም፡ ምክንያቱ ብርሃን የምታገኘው፡ ከጸሐይ ዘንድ በሁለተኛ ደረጃ ነውና። አሁን፡ እንደ ባልና ሚስት፡ ፀሐይና ጨረቃ፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን እና ክርስቶስ ናቸው።

35 እንግዲህ፡ እነዚህ ነገሮች፡ የክርስቶስ ጥላ ሆነው እናገኛቸዋለን። በብሉይ ኪዳን ያሉት መስዋዕቶች ሁሉ፡ በዓላት፡ እና ሁሉም ነገሮች፡ ወለል ላይ ተዘርግቶ እንደሚታይ፡ እንደ ጥላ የክርስቶስን ጥላ ናቸው። አሁን ትክክለኛውን የአምልኮ ስፍራ ማግኘት ያለብን እዚህ ላይ ነው፡ በብሉይ ኪዳን ወደተሰጠበት ወደዚህ ተመልሰን እነዚያ ነገሮች ምን እንደነበሩ ማየት ነው።

36 አሁን፡ ጥላ ወለል ላይ ሲታይ፡ ጥላውን ወለሉ ላይ ስለጣለ፡ ወንድ ይሁን፡ ሴት፡ ወይም እንስሳ፡ ወይም ምንም ነገር መለየት ትችላላችሁ። እና ያ ጥላ እያጠረ ሲሄድ፡ ጥላው ነጌቲቭ ስለሆነ፥ ደግሞም ያለ ፖዘቲቭ ነጌቲቭ ሊኖር አይችልም። ስለዚህ፡ ፖዘቲቩ ወደ ነጌቲቩ በተጠጋ ቁጥር፡ ነጌቲቩ በፖዘቲቩ ይዋጣል። ጥላው እና—ፖዘቲቩ አንድ ስፍራ ላይ ይሰበሰባሉ፡ ፖዘቲቭ ነው የሚያስብለውም ያ ነው።

ስለዚህ መጽሐፍ ደግሞ እንደሚል፡ “ብሉይ ኪዳን ለሚመጡ ነገሮች፡ የነገር ጥላ ነው፡” ስለዚህ “ሌሎች የብሉዩ ነገሮች” እንዲህ ከሆኑ፡ እንግዲያውስ ክርስቶስም ሊመጡ ላላቸው ነገሮች ጥላ ነበር።

37 ስለዚህ ከብሉይ ኪዳን ጥላዎች፡ ስሙ ያኖረበትን ስፍራ፡ ማየት እንችላለን፡ ይህም... አሁን ነው። አሁን፡ እንደ ጥላ... ወለሉን ሲሻገር፡ እንደተናገርኩት፡ ጥላ በመሆኑ፡ ነጌቲቭ ነው፡ ስለዚህ እኛ፡ አምልኮ አቅራቢዎቹ፡ የብሉይ ኪዳን ጥላዎች ወደ አዲሱ ፖዘቲቭ ሲዋሃዱ ማየት እንችላለን።

38 አሁን፡ በዓላት በሙሉ፡ አውደ አመቶች ሁሉ፡ ድንኳኑ ሁሉ፡ እንጨቶች በሙሉ፡ በድንኳኑ ውስጥ የነበሩ ነገሮች፡ እያንዳንዳቸው የክርስቶስ ጥላ ናቸው። መሰዋዕቶች ሁሉ፡ ሕጎች በሙሉ፡ እያንዳንዱ ነገር የክርስቶስ ጥላ ነበሩ። ከጊዜ ወደ ጊዜ፡ በዚህ በተበርናክሉ ውስጥ፡ ተምረናቸዋል።

በዚህም ምክንያት፡ እያንዳንዱ የእምነት መግለጫ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ እና የሐይማኖት ተቋም ሁሉ፡ ተራ መሆናቸውን እንገነዘባለን። በሩጫው ውድድሩ ውስጥ፡ በጭራሽ አይታሰቡም። እያንዳንዱ የሃይማኖት መግለጫ፡ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን፡ እያንዳንዱ የሐይማኖት ተቋም፡ ሙሉ በሙሉ ተገልፏል። ለእነርሱ የሚሆን ስፍራ በጭራሽ የለም።

39 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ የባቢሎን ግንብ ለመስራት በኃይል ከተገደዱበት አንድነት በቀር፡ በብሉይ ኪዳን፡ የቤተ ክርስቲያን ጥላ የትም አይታይም። የአንድነታቸው ብቸኛው ጥላ ያ ነው። ምክንያቱም፡ ይህ ኒምሮድ የተባለ፡ እጅግ ክፉ ሰው ወጥቶ ሁሉንም ትናንሽ አገሮች ወደ አንድ ቦታ እና ወደዚህ ታላቅ ግንብ እንዲሰበሰቡ ያስገደዳቸው እሱ ነው። እርግጥ ነው፡ ሃይማኖታዊ አምልኮ ነበር፡ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ግን ግምት ውስጥ አይገባም። ስለዚህ የባቢሎን ግንብ፡ በብሉይ ኪዳን፡ የሃይማኖት ተቋም ጥላ ነበረ። ማለት፡ ይህ ሃይማኖት በእርግጥ ሃይማኖት ነበር፡ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ሃይማኖት አልነበረም።

40 እግዚአብሔር ስሙን በየትኛውም የሐይማኖት ተቋም ውስጥ ማስቀመጥ አልመረጠም። ከሆነ ግን፡ ቃል አምጡልኝ። መርጧል ብለው ይናገራሉ፡ ቢሆንም ግን አልመረጠም። ስሙን በአንዲት ስፍራ አኖራለሁ ብሎ ስለተናገረ፡ ስሙን በብዙ ቦታዎች ማስቀመጥ አይችልም። እና፡ ያቺ ስፍራ፡ እያንዳንዳቸው የሐይማኖት ተቋሞቻችን እኛ ነን ለማለት ይፈልጋሉ፡ ነገር ግን በተቃራኒው ነው።

እንግዲያውስ ስሙን ያኖረበት ስፍራ የት ይሆን?

41 ስለዚህ፡ አሁን፡ በመጀመሪያ፡ እሱ ራሱ ስሙ፡ ማን ነው? እርሱ በስፍራው ያስቀመጠውን ነገር ምን እንደሆነ ከማግኘታችን በፊት (ስሙ) የእግዚአብሔርን ስም ማን እንደሚባል መፈለግ አለብን።

አሁን፡ ብዙ መገለጫዎች እንደነበሩት እናውቃለን። እንዲህ ይባላል... እንዲህም “አባት” ተባለ፡ ይህም መገለጫ ነው። ደግሞም “ልጅ” ተባለ፡ ይህም መገለጫ ነው። “መንፈስ ቅዱስ” ተብሏል፡ ይህም ደግሞ መገለጫ ነው። “የሳሮን ጽጌሬዳ” ተባለ፡ ይህም መገለጫ ነው። “የሸለቆ አበባ፡” መገለጫ ነው፡ “የማለዳ ኮከብ።” “ጆሆቫ-ጂሬህ፡ ጆሆቫ-ራፋ፡” ሰባት የተያያዙ፡ ልዩ ልዩ፡ የመቤዠት ስሞች ናቸው፡ ሁሉም መገለጫዎች ነበሩ። አንዳቸውም ስም አልነበሩም።

ስም ግን አለው።

42 ሙሴን ባገኘው ጊዜ፡ ገና ስም አልነበረውም፡ ለሙሴም፡ “ያለና ይሚኖር
እኔ ነኝ” አለው። ኢየሱስም በምድር ላይ ሰናየው፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 6 ላይ ሲናገር... ይቅርታ አርጉልኝ፡ ቅዱስ ዮሐንስ 6ኛው ምዕራፍ ላይ። “ያለና የሚኖር እኔ ነኝ፡” ብሏል።

እነሱም እንዲህ አሉት “ለምን፡ አንተ ከሃምሳ ዓመት በላይ አይደለህም፡ እና ‘አብርሃምን አይቻለሁ፡’” ትላለህን?

43 እሱም “አብራሃም ከመኖሩ በፊት፡ እኔ ነኝ፡” አላቸው። እና “እኔ ነኝ”
ደግሞ፡ በሚነደው ቁጥቋጦ ላይ የነበረው አካል ነው፡ በሙሴ ዘመን በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ የነበረው የእሳት ዓምድ፡ “ያለና የሚኖር እኔ ነኝ” የሆነው ነው።

44 አሁን ደግሞ፡ ኢየሱስ “እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡
አልተቀበላችሁኝምም፡” ሲል እንመለከተዋለን። እንግዲያውስ፡ የአብ ስም ኢየሱስ መሆኑ ግድ ነው። በትክክል። የአብ ስም ኢየሱስ ነው፡ ምክንያቱም ኢየሱስ ተናግሯል። “የአባቴን ስም ይዣለሁ። በአባቴ ስም መጥቻለሁ፡ አልተቀበላችሁኝምም።” ስለዚህ፡ ስሙ ኢየሱስ ነበር።

ገብርኤልም ኢየሱስ ብሎ ጠርቶታል፡ ነቢያት ኢየሱስ ብለው ጠሩት፡ እርሱም ፍጹም ኢየሱስ ነው። ከመወለዱ በፊት፡ ቅዱሱ ነቢይ እንኳ ስሙን **አማኑኤል** ብሎ ጠራው፡ ትርጓሜውም፡ “እግዚአብሔር ከኛ ጋር” ማለት ነው። ከዚያም፡ “የዓለምን ኃጢአት ያሰወግድ ዘንድ፡ እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠ፡” በመገለጡ፡ ምክንያትም፡ ኢየሱስ የሚባል ስም ተሰጠው። ስለዚህ፡ ስሙ ኢየሱስ ነው።

ያ ስም ደግሞ በአንድ ሰው ውስጥ አሰቀመጠው፡ እንጂ በቤተ ክርስቲያን አይደለም፡ በሐይማኖት ተቋም አይደለም፡ በሐይማኖት መግለጫ ውስጥ አይደለም፡ ነገር ግን በአንድ ሰው ላይ! ስሙን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማኖር መረጠ። ስለዚህ አሁን እርሱን የምታመልኩበት፡የእግዚአብሔር የአምልኮ ስፍራ እሱ ሆኖ እናገኘዋለን።

45 ገና ከመወለዱ በፊት፡ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ። እጅግ አስፈላጊ
ስለነበረ፡ በመልአኩ ገብርኤል ለእናቱ ተሰጣት፡ ይህም ስሙ እንዲሁ ነበርና “የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ፡” ተብሎ ይጠራ ዘንድ ነው።

46 ይኸው፡ አሁንም ከእኛ ጋር አለ። ይህ፡ ብቻውን ነው። እግዚአብሔር፡ ለራሱ
የመረጠው የአምልኮ ስፍራ፡ ይኸው ነው። የተመረጠ፡ የእግዚአብሔር ስፍራ። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ለመገናኘት የመረጠው፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይደለም፡ በሐይማኖት ተቋም ውስጥ አይደለም፡ በሐይማኖት መግለጫ ውስጥ አይደለም፡ በክርስቶስ ውስጥ ነው። እግዚአብሔር ከሰው ጋር የሚገናኝበት እና እግዚአብሔርን የሚያመልክበት ብቸኛው ስፍራ፡ በክርስቶስ ውስጥ ነው። ብቸኛው ስፍራ እሱ ነው። ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት፣ ምንም ሁን ማንም፡ እግዚአብሔርን በትክክል ማምለክ የምትችሉት አንድ ቦታ ብቻ ነው፡ እርሱም በክርስቶስ ነው።

ሮሜ 8:1፣ እንዲህ ይላል፡ “እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፡ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ፡ እንደ ሥጋ ፈቃድ አይሄዱምና።” ወንጌል ይህ ነው።

47 በሐይማኖት መግለጫ ምክንያት ልንለያይ እንችላለን። በሰው-ሰራሽ አሳቤዎች ልንለያይ እንችላለን። ወደ አንድ የሜቶዲስት ቤት ክርስቲያን ስትቀላቀሉ፡ ሜቶዲስት መሆን ይጠበቅባችኋል፡ በባፕቲስት፡ ባፕቲስት፡ በካቶሊክ፡ ካቶሊክ ትሆናላችሁ። ነገር ግን አንዴ ወደ ክርስቶስ አካል ተጠምቃችሁ፡ የአካሉ ብልት ስትሆኑ ግን፡ ልዩነት የለም። በክርስቶስ ኢየሱስ ስለሆናችሁ፡ በመካከል የክፍፍል ግድግዳዎች ፈርሰዋልና ነፃ ናችሁ። በክርስቶስ ኢየሱስም ስትሆኑ እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ታመልኩታላችሁ። በክርስቶስ ኢየሱስ እንድታመልኩት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

48 ስለዚህ፡ የትኛይቱ የሐይማኖት ተቋም እኔ ነኝ ማለት አትችልም፡ ማንም ቢሆን እኔ ነኝ ማለት አይችልም። ነኝ ማለታችሁ እንዴት ብትደፍሩ ነው? እንደዚህ ያለ ነገር ማድረግ ይህን ከእርሱ መውሰድ ማለት፡ ከክርስቶስ ተለይታችሁ፥ የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ መሆን ማለት ነው። ይህን ማድረግ አትችሉም። እግዚአብሄር አምልኮ አቅራቢውን የሚገናኝበት ብቸኛው ስፍራ ክርስቶስ ነው።

49 ዛሬ፡ እንዲህ ይላሉ። እንዲህ የሚሉኝ ሰዎች ገጥመውኛል። በቅርብ ጊዜ አንድ ሰው፡ ከቤውመንት ቴክሳስ፡ ደወለልኝ። እና እንዲህ አለኝ፡ “አቶ ብራንሃም፡ ስምህ በቤተ ክርስቲያናችን መዝገብ ላይ ካልሰፈረ፡ ወደ አገነት አትገባም አለኝ።” እንዲህ ያለ ነገር አስባችሁ ታውቃላችሁ? እንደዚያ ያለውን ነገር አትመኑት። የዚያች ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አለብህ ወይም ወደ መንግሥተ ሰማያት መሄድ አትችልም ብለው ያስባሉ። ያ ስህተት ነው። ያንን ማመን፡ የክርስቶስ ተቃዋሚ መሆን ነው። ይህን እላችኋለሁ፥ እንዲህ ያለውን መንፈስ ካመናችሁ፡ ጠፍታችኋል። የመጥፋታችሁ ትክክለኛ ምሳሌ ነው፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ካደረገው ነገር ያሰወጣችኋል። እግዚአብሔር ስሙን በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ውሰጥ አላኖረም። ያኖረው እሱ እና ልጁ አንድ ስለሆኑ፡ በልጁ፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ትክክለኛው የአምልኮ ስፍራ ያ ነው። ሌላ መሠረት፡ ሌላ ድንጋይ አልተጣለም።

በጠንካራው ዓለት፡ በክርስቶስ ላይ፡ ቆሜአለሁ፡<br>ሌላው ሁሉ የሚያስምጥ አሸዋ ነው።

የሐይማኖት ተቋማት ወድቀው ይፈራርሳሉ፡ ሕዝብ ያልፋል፡ እርሱ ግን ለዘለአለም እንደጸና ይኖራል። በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆነ በቀር፡ ሰው እግዚአብሔርን የሚያመልክበት፡ እግዚአብሔርም መልሱን የሚመልስለት ስፍራ፡ ለሰው ሌላ የለውም። እግዚአብሔር ስሙን ሊጠራበት የመረጠው ብቸኛው ቦታ፡ ይህ ብቻ ነው፡ ሰው እርሱን ያመልክ ዘንድ፡ ከሰው ጋር የሚገናኝበት ብቸኛው ቦታ ይህ ብቻ ነው። ከዚህ ሌላ ማመን፡ መጥፋት ነው።

50 ሰባቱም የአይሁድ በዓላት በአንዲት ስፍራ ይደረጉ እንደነበር፡ ልብ በሉ። አንዱን በዓል ለሜቶዲስት **በዚያ** ስፍራ፡ አንዱም ለባብቲስት **በዚህ** ስፍራ፡ አንደኛውም ለፕረስቢተሪያኖች **በዛኛው** ስፍራ፡ ለካቶሊክም **በዚህ** በኩል፡ አንዱም ለፕሮቴስታንት በጭራሽ አልነበረም። ሰባቱም በዓላት በአንድ ቦታ ይደረጉ ነበር።

51 ለዚህ የሚሆን ትክክለኛ ጥላው ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት በቃሉ እንደሚጠብቅ ለማሳየት፡ ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት ተምረናቸዋል፡ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ከቃሉ ከፍሎ ያፈራ ነበርና፡ ባፈሩ ቁጥርም ብርሃን ያያሉ።

ከዚያም ልክ በኢየሱስ ስም መጠመቅን ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳገኙት ሰዎች ይሆናል። ምን አደረጉ? በዚያ ዙርያ የሐይማኖት ተቋም መሰረቱ፡ ወድያውኑ ሞተ። ከዚያም እግዚአብሔር ወደ ሌላ ሰው ተሻገረ። በሃይማኖት መግለጫዎች እና ዶግማዎች በማናቸውም ውስጥ አይቆይም። ከዚያ ጋር ጉዳይ የለውም። እግዚአብሔር የተበላሸ ነገር የለውም። የእግዚአብሔር ቃል ቅዱስና፡ ያልተነካካ ነው። ክርስቶስ የእግዚአብሔር የአምልኮ ማዕከል ነው። እርሱ አምላክ ነው።

52 ሰባቱም በዓላት በዚህ አንድ ቦታ መቀመጥ አለባቸው። በዓሉን በሌላ ቦታ ማድረግ አትችሉም። ሰባቱም፡ ሰፍራቸው... የዓመቱ ሰባት በዓላት በአንድ ሰፍራ መሆን አለባቸው። ስለዚህ፡ ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናትም ከዚያ ከአንዱ ቦታ መምጣት ነበረባቸው፡ ያም በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የሚናገረው ራሱ ክርስቶስ ነው። ይህ በትክክል እውነት ነው። የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፡ ጥላ፡ ይሁን እንጂ ከዚያ ነገር ውስጥ የሐይማኖት ተቋም መሰረቱበት።

53 አሁን ከዚህ ሳንወጣ ሌላ ጥላ ደግሞ እንመልከት፡ ይህም፡ ኢየሱስ የሚታይበት ጥላ፡ የፋሲካ ጥላ ነው። እዚህ ላይ በሞት የሚሆን፡ የደም መሰዋዕትነትን እናያለን። ይህም ስለ ክርስቶስ ጥላነት የሚደረግ የደም መሰዋዕት ነበር። የሐይማኖት ተቋም ይደማል'ዴ፡ የምትደማ ቤተ ክርስቲያን እስኪ አሰቡት፡ የምትደማ የሐይማኖት ተቋም? በእርግጠኛነት የለችም። ከሕይወት ይደማ ዘንድ፡ ደም አስፈለገ። ስለዚህ፡ ሕይወት፡ እዚህ ጋር ኢየሱስ በበግ አምሳል መጣ። በጉ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር፡ እና ስለ ክርስቶስም ጥላ ነበረ፡ ምክንያቱ እርሱ ዮሐንስ ያስተዋወቀው "የዓለምን ኀጢአት የሚያሰወግድ፡" "የእግዚአብሔር በግ፡" እሱ ነበረ። እዚህ በዘፀአት ምዕራፍ 12 ላይ፡ ኢየሱስ ወደ ትዕይንት ሲመጣ እናየዋለን።

54 ልብ በሉ፡ ይህ ሰፍራ ሞት ሊነካው ያልቻለ ብቸኛ ሰፍራ ነበር። ሞት ምድሪቱን ሊመታ በመጣ ጊዜ፡ አንድ የተለየ ሰፍራ ነበር፥ ከዚህ ውጪ የሆኑ ሞቱ። አንድ ሰፍራ ብቻ! ይህ ማለት፡ አንድ ቤት ነበረች ማለት አይደለም፥ አንድ ቦታ ግን ነበረች፡ ያም ቦታ በጉ የሚሞትባት ሰፍራ ናት። የበጉ ደም ባለበት ቦታ፡ የሞት መልአክ ሊመጣ አይችልም፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ስሙን ያስቀመጠበት ብቸኛ ቦታ ነው። በጉም፡ የበግ ጠቦት ተብሎ በዚያ መጠራት ተጀመረ። ልብ በሉ፡ ሞት ሊመታው ያልተቻለው ብቸኛው ቦታ ይህ ነው።

55 አሁን ዛሬም ተመሳሳይ ነው። መንፈሳዊ ሞት የማይመታው አንድ ቦታ ብቻ አለ፡ እርሱም ቃሉ ነው። ቃሉ ህያው ቃል ስለሆነ፡ ሞት አይነካውም።

የሐይማኖት መግለጫዎች ሰትጨማምሩበት ግን፡ ቃሉ ተለይቶ ይወጣል። እንደ ውሃ ከዘይት ይለያል። አንድ ላይ መቀላቀል አይችሉም። ስለዚህ፡ እያችሁ፡ የሐይማኖት መግለጫው ወደ ሐይማኖት ተቋሙ ሲገባ፡ ሁሉም የሐይማኖት መግለጫውን ይከተሉታል፥ ቃሉም ከዚያ ተለይቶ ይወጣል፡ ከሌላ ሰው ጋር

ይሄድና ራሱን ያሳድጋል። ከመጽደቅ ወደ መቅደስ፡ ከዚያም፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሲጓዝ፡ ፍትነቱን እየጨመረ ይሄዳል፡ ከዚያም ዘር ወደ መሆን ያድጋል! እግዚአብሔር የሚጓዝበት እርግጫ ይታያችኋልን? እርሱ ቃል ነውና፡ ስሙን፡ ሁልጊዜ በተመሳሳይ መንገድ፡ ያመጣዋል።

ልብ ይበሉ፡ ሊሞት አይችልም። የሕይወት ቃል ሊሞት አይችልም።

56 አሁን፡ ምን ያህል ፍጹም እንደሆነ አስተውሉ። የሞት መልአክ የግብፅን ታላላቅ ምሁራን እንዳይመታ አልተከለከለም ነበር። የተቀደሱ መሬቶቿን፡ ታላላቅ ህንጻዎቿን፡ ፈርዖኖቿን መምታት አልተከለከለም። ወይም፡ የምድሪቱ ካህናት፡ መልአኩ እንዳይመታ አልተከለከለም ነበር። የትኛውንም ሕንፃ፡ የትኛውም ቦታ፡ ማንንም ሊመታ ይችላል፡ በጉ ባለበት ቦታ ግን መምታት አይችልም።

ይህ እግዚአብሔር የመረጠው እና በጉ ያለበት ስፍራ፡ ሞት ሊመታው አይችልም።

57 ልብ በሉ፡ እንዲሁም እንዲህ አይደለም… እስራኤልን ወይም የዕብራዉያን ክሃናት፡ ወይም፡ የሐይማኖት ተቋሞቻቸን አትምታ አልተባለም። ሁሉም እግዚአብሔር በመረጠው፡ በተዘጋጀው ቦታ ይሆናሉ፡ ካልሆነ በሞት ይቀሰፋሉ።

58 ቤተ ክርስቲያን ሆይ፡ የትም ብትሆኚ፡ የማንምም አባል ብትሆኚ፡ ምንም ልዩነት አይፈጥርብኝም። ነገር ግን፡ ማወቅ ያለብሽ አንድ ነገር አለ፡ ወይ በክርስቶስ ሁኚ ወይም ትሞቻለሽ። ከእሱ ውጭ መኖር አትችሉም። ህንጻችሁ፡ እንደ ቤተክርስቲያን ምንም ችግር ላይኖረው ይችላል፥ እንደ ሰውም፡ አምልኮአችሁ ችግር ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን አካሉን፡ ደሙን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ስትክዱ ግን፡ በካዳችሁበት ቅጽበት ሞታችኋል። እግዚአብሔር የመረጠው የማምለኪያ ስፍራ ነው። ሰሙ፡ በትክክል ያለበት ቦታ ነው። ስሙን ለማስቀመጥ የመረጠው እዚያ ነው፥ በቤተ ክርስቲያን ሳይሆን፡ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

59 አስተውሉ፡ ደህንነት እርሱ በመረጠው ስፍራ፡ በበጉ ዘንድ፡ እና በበጉ ስም ዘንድ ብቻ ይገኛል።

60 ልብ በሉ፡ በጉ “ተባት” ነበረ፡ እሱ ነው፡ ሴት አይደለም። እሷ፡ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፥ የእሱ ሰም ነው፡ ሰሟ አይደለም። ህዝቡን ሊገናኝ የሄደበት በሰሟ ሳይሆን፡ በሰሙ፡ እርሱ፡ በጉ ነው!

61 እኛ እንዲህ እንላለን፡ “ቤተ ክርስቲያን፣ ታላቂቱ፣ ኃያሏ ቤተ ክርስቲያን፡ **ይህን** አደረገች **ያንንም** አደረገች። ማዕበሉን የሰፈረች። በህዝብ ብዛት ተጥለቀለቀች። በቁጥር በጣም ብዙ ነን። እኛ ብርቱ ቤተክርስቲያን ነን። እሷ ታላቂቱ ነች።”

እግዚአብሔር ግን እሷ ብሎ ተናግሮ አያውቅም። “እሱ፡” እንጂ። መሰብሰቢያው ሰፍራ፡ “እሱ” ነው፡ በጉ ነው፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ አይደለችም። ሰሙ እንጂ፡ ሰሟ አይደለም። ሰሟን የትም አላስቀመጠም። ሰሙን ግን “በእሱ” ዘንድ አኖረው!

በዚህ መንገድ፡ “የምናደርገው ነገር ሁሉ፡ በስራም በቃልም፡ ሁሉንም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማድረግ አለብን።” ብንጸይ፡ በኢየሱስ ስም መጸለይ አለብን። ንሰሓ ብንገባም፡ በኢየሱስ ስም መሆን አለበት። ብንጓዝ፡ በኢየሱስ ስም እንጓዝ። ብንናገር፡ በኢየሱስ ስም እንናገር። ስንጠመቅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ አለብን። ምክንያቱ፡ “በቃልም ሆነ በስራ የምታደርጉትን ሁሉ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አድርጉት።”

62 አንድ ባልደረባዬ አንድ ጊዜ ነገሩን ሲወያይ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ባለቤቴ፡ እኔ... ” እንዲህ አለ፡ “እሷ፡ ስሟ **እከሊት-እና-እከሊት** ትባላለች።” አገልጋይ ነው፡ ምናልባት ዛሬ እዚህ ሊሆን ይችላል። እና እንዲህ አለ፡ “ሚስቴ፡” “ስሜን ተሸክማለች፡” አለኝ። ስሙን **ጆንስ** ልበለው፡ ጆንስ ግን አይደለም። እንዲህ አለ፡ “እንግዲህ፡ በየማለዳ እየተንሳች፡ መጥረጊያውን ይዛ መጥታ እንዲህ ማለት አይጠበቅባትም፡ ‘አሁን ወለሉን በጆንስ ስም እጠርጋለሁ፡ እና ሳህኖቹን በጆንስ ስም አጥባለሁ፡ ልብሶቹም በጆንስ ስም እሰፋለሁ ማለት አያስፈልጋትም።’” “ምንም አይነት ስም መጥራት ያሌብህ አይመስለኛም፡” አለኝ።

“አለብህ ብዬ አምናለሁ፡” አልኩት። በትክክል።

እርሱም “አይ፡ ለምን? መናገር አይጠበቅባትም። ሲጀመርም፡ የምትሰራው ነገር ሁሉ በጆንስ ስም ነው፡” አለኝ።

63 እኔም አልኩት፡ “ይሁን እንጂ ወደ ጎዳናው ወርደህ አግኝተሃት፡ ‘ነይ፡ ጆንስ፡” ብለህ አላመጣሃትም። በመጀመሪያ፡ በሰርዓት፡ በጋብቻ ሥነ ሥርዓት፡ ‘ጆንስ፡’ መሆን ይኖርባታል። ካልሆነ ግን፡ በምንዝርና እየኖርክ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ካልሆነ በቀር በሌላ መንገድ ከተጠመቃችሁ፡ ይህ የዝሙት ጥምቀት ነው፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለምና።”

ስለዚህ፡ “በቃልም ሆነ በስራ የምታደርጉትን ሁሉ፡ በኢየሱስ ስም አድርጉት።” ከዚያ በኋላ፡ ምን ታደርጋለህ! በመጀመሪያ ግን፡ በስሙ ሆናችኋል።

64 ዛሬ ማታ በዚህ ሕንፃ ውስጥ፡ ብዙ መልከ መልካም ሴቶች አሉ፡ መልከ መልካም፡ ታማኝ ሴቶች፥ ይሁን እንጂ ወይዘሮ ዊልያም ብራንሃም ግን አንድ ብቻ አለች። ከእኔ ጋር ወደ ቤት የምትሄደው እሷ ነች። ባለቤቴ የሆነችው እሷ ነች።

65 በዓለም ውስጥ ጥሩ ሰዎች አሉ፡ ጥሩ አብያተ ክርስቲያናትም አሉ፡ ይሁን እንጂ ወይዘሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አንድ ብቻ አለች፡ የሚመጣውም ወደሷ ነው። ስሙ ያኖረባትም እሷ ናት። አምልኮው ያለበትም በዚያ ውስጥ ነው፡ በሷ እና በሷ ብቻ። ይህ እውነት ነው። ኦህ፡ አዎን፡ ጌታዬ። እውነት እንደሆነ አውቀናል።

66 አሁን፡ ለዛ ነው፡ ሁላችንም፡ “በቃልም ሆነ በስራ የምናደርገውን ሁሉ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናደርገዋለን።”

“ለመዳን ከሰማይ በታች የተሰጠ ሌላ ስም የለም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ እንጂ።” የሐዋርያት ሥራ፡ ምዕራፍ 2 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ “ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን... ” “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ በቀር፡ ሰው መዳን

ያለበት ከሰማይ በታች የተሰጠ ሌላ ስም የለም።” አሜን። እንደምትረዱት ተሰፋ አደርጋለሁ። የኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ሁሉም…

በከፍታው በሰማይ ያለው ሁሉ በሱ ተሰይሟል፡ “በሰማይ ያለ ቤተሰብ ሁሉ ኢየሱስ ተብሏል፡” ይላል መጽሐፍ ቅዱስ፡ “በምድር ላይ ያለው ቤተሰብ ሁሉም ኢየሱስ ይባላል።” ስለዚህ እግዚአብሔር ስሙን ያስቀመጠበት ያ ነው የመረጠውም ያ ነው። የማምለኪያ ሰፍራው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ነው። አሁን፡ እንደዚያ እንዲሆን፡ ከእርሱ በቀር ሌላ ምንም ቦታ እንደሌለ እናውቃለን።

67 “ሊድኑበት የሚገባበት፡ ለሰው የተሰጠ ሰም ከሰማይ በታች ሌላ የለም።” የእግዚአብሔር የቤዛነት ሰም የእርሱ ነው። እግዚአብሔር ጆሆቫ-ጂሬ፡ ጆሆቫ-ራፋ የተባለ ሰም አለው። **ጆሆቫ-ጂሬ፡** “ኃጢአትን ሁሉ ይቅር የሚል ጌታ።” **ጆሆቫ-ራፋ፡** “ጌታ ደዌህን ሁሉ ይፈውሳል።” ብዙ መገለጫዎች አሉት። ይሁን እንጂ አንድ የቤዛነት ሰም አለው፡ ያም የሰው ዘር ሁሉ ሰም ነው፡ ሰሙም “ኢየሱስ” ይባላል። ሰሙ ያ ነው፡ ማኖር የወደደው እሱን ነው። ያኖረውስ የት ነው? በክርስቶስ ውስጥ አኖረው።

68 ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሰሞች፣ የሃይማኖት መግለጫዎች፣ መጠሪያዎችን፣ እነዚህን ሁሉ ማመን ሞት ነው። የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንዲወስድህ ታምነህ ከሆነ፡ ጠፍተሃል። የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድትወስድህ፡ በጴንጤዎች ታምነህ ከሆነ፡ ጠፍተሃል። እና በባፕቲስቶች፡ ሉተራን፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ በካቶሊክ፡ እና በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት፡ በሰሞቻቸው፡ ወይም በመጠሪያዎቻቸው፡ ወይም በሐይማኖት መግለጫዎቻቸው ከታመንክ፡ ጠፍተሃል።

ምክንያቱ፡ በመሰረቱ’ኮ ወደ ማምለኪያው ካልቀረብክ በስተቀር ማምለክም አትችልም። አሜን። እግዚአብሔር ከአምላኪው ጋር የሚገናኝበት ብቸኛው ሰፍራ፡ ሰሙን ለማስቀመጥ በመረጠው ሰፍራ ላይ ነው። ሌሎቹ ሁሉ፡ ብትታመንባቸው፡ ትጠፋለህ። እሱም…

69 እዚህ ላይ ሌላ የኢየሱስ ጥላ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ፡ አሰምሬበታለሁ። እዚህ ጋርም፡ በ—በጥላ ይታያል፡ “ነውር የሌለበት ሊሆን ይገባል።” ሰሙን ያስቀመጠበት ሰፍራ፡ ማለት ይህ በግ ነውር የሌለበት መሆን አለበት።

እንግዲያውስ፡ ይህንን በየትኛው ቤተ እምነት ወይም ስርዓት ላይ መጠቆም ትችላላችሁ፡ የትኛው ቤተ ክርስቲያን፡ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት፣ አይሁድ፣ ምንም ይሁን ምን? የትኛው ስርዓት፡ የትኛው ቤተ እምነት፡ “ነውር አልባ” ብላችሁ፡ የትኛው መጠቆም ትችላላችሁ? ሁሉም የወደቁ፡ የተተዉ ናቸው!

አንዲት ሰፍራ ግን አለች! ሃሌሉያ! እሷም በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ናት። በእርሱ ዘንድ ነውር የለም። በእርሱ ዘንድ ምንም ጥፋት የለም።

ይህን መጠቆም አትችሉም። ቤተ ክርስቲያናቸው ጥፋት እንደሌለባት፡ **እንዲህ** እና እንዲያ ለማለት የሚዳዳቸው ሰዎች አሉ። እርኩሰት ነው፡ ውል-አፍራሾች፡ ናፋቂዎች፡ በከፊል የሞቱ፡ ሎዶቅያ፡ የሐይማኖት መግለጫ ነው እንጂ፡ እውነት አይደለም። ነገር ግን፡ ራሱ ጠላቱ፡ ጲላጦስ እንኳ “በእርሱ ላይ ምንም ጥፋት አላገኘሁም፡” ብሏል። የገዛ ጠላቱ ምንም ጥፋት እንደሌለበት መሰክሮለታል። በእርሱ ላይ ምንም ኃጢአት መጠቆም አትችሉም።

70 በዘመኑ የነበሩትን ካህናት እንዲህ አላቸው፡ “ከእናንተ በኃጢአት የሚከሰኝ ማን ነው? ኃጢአተኛ መሆኔን የሚያሳየኝ ማን ነው? ”

ምንም ስህተት ሰርታ አታውቅም የምትባል አንዲት ቤተክርስቲያን ንገሩኝ። በእውነቱ፡ አታገኙም፡ በቀን መቁጠሪያው ውስጥ፡ ሊደረጉ የሚችሉ ሁሉ ግድያዎች ሁሉ ያላደረገች፡ በጭራሽ አታገኙም። በዚህ ሁሉ ግን ስለራሳቸውን ይመሰክራሉ... ስለዚህ የእግዚአብሔር የአምልኮ ሰፍራ፡ በሐይማኖት መግለጫ ወይም ቤተ እምነት ሊሆን አይችልም።

71 ወዳጆች ሆይ፡ ሰሜታችሁን መጉዳት አልፈልግም፡ ይሁን እንጂ ስለዚህ መልእክት ኃላፊነት አለብኝ፡ እንግዲህ፡ መልእክቱም፡ “ከዚህ ግራ መጋባት ውጡ ነው!” ውጡ ካልኳችሁ፡ ወዴት እወስዳችኋለሁ? ወደ ብራንሃም ተበርናክል ነውን? ከሌሎቹ ባልተናነሰ መልኩ ጥፋተኛ ነው።

ነገር ግን ከሞት የምትድኑበት አንድ የተጠበቀ ሰፍራ አለ፡ ወደዚያም እወስዳችኋለሁ፡ ያም በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ነው፡ እሱ የእግዚአብሔር የአምልኮ ሰፍራ ነውና። እግዚአብሔር ሰሙን ያሰቀመጠበት፡ ዛሬ ማታ፡ የማስተዋውቃችሁ ሰፍራ ያ ነው። ወደዚያ የሚገቡትን ሁሉ እንደሚያገኛቸው ቃል የገባለት ሰፍራ ነው፡ በዚያም ከእርሱ ጋር ያመልካል ይበላልም፡ ያም በክርስቶስ ነው፥ በቤተ ክርስቲያን አይደለም፡ በተብርናክል አይደለም።

ነገር ግን፡ በክርስቶስ፡ እርሱ የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው። እርሱ ራሱ፡ እግዚአብሔር የገባበት፡ እና በእርሱ ያደረበት ሰፍራ ነው። “በእርሱ ልኖር ደሰ የሚለኝ፡ የምወደው ልጄ ይህ ነው።” እግዚአብሔር ያደረበት፡ ሰሙን አምጥቶ ያኖረበት ሰፍራ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ፡ ሰሙ በአንድ ሰው፡ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ እሱ ራሱ ባደረበት፡ በዚያ ድንኳን ውስጥ ተቀምጧል።

በዚያም፡ በጥላ፡ ጥንታዊቷ ኢየሩሳሌም፡ የጥንቱ በዓላት፡ ጥንታዊው ቤተ መቅደስ ውስጥ፡ ጥላ ነበረ፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ በገባ ጊዜ፡ እና አርፎም በተቀመጠ ቀን፡ ዕጣኑ ሲገባ፡ የእግዚአብሔርም ድምፅ ከእርሱ ይሰማ ነበር።

እንዲሁም ደግሞ የእግዚአብሔርም ድምፅ፡ ወደ ድንኳኑ፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ ይሰማል፥ እእሱም፡ ጥንታዊው (ፍጥረታዊው) ሊመጣ ላለው የአዲሱ ነገር ጥላው ነበረ። ወደ ክርስቶሰም በመጣ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ “በእርሱ ልኖር ደሰ የሚለኝ፡ የምወደው ልጄ ይህ ነው። እነሆም ሰሜን የማሰቀምጥበት፡ እና ሰው ጋር የምገናኝበትን፡ የምሰግድበትንም ሰፍራ እመርጣለሁ።” እግዚአብሄር ሰፍራውን መረጠ፡ በቤተ ክርስቲያን በሐይማኖት ተቋም አይደለም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ እንጂ። አዎን፡ ወዳጄ።

72 እንደተናገርኩትም እርሱ፡ “ነውር የሌለበት” መሆን አለበት። ይህ እኛ ነን ሊል የሚችል የእምነት ተቋም የለም። ነን ካሉ ግን፥ ጸረ ክርስቶስ ናቸው።

73 አሁን እዚህ እንደምናየው፡ አሁንም ጥላውን እንደገና ተመልከቱ። በ—በጉ ሊጠበቅ ይገባዋል። አሁን፡ ማሰታወሻ ለምትይዙ፡ ይህ በዘጸአት 12 ላይ ታገኙታላችሁ፡ ዘጸአት 12፡3 እስከ 6 ድረስ። ጠቦቱ ገና ወደ መሰዋዕቱ መሄድ ተገቢ መሆኑን ለማየት፡ ለመፈተሽ፡ ለአራት ቀናት መቆየት አለበት። ለአራት ቀናት፡ ተጠብቆ፡ በላዩ ላይ ነውር እንዳለ ለማየት፡ ደጋግሞ ይመረመራል፡ በውስጡም በሽታ ካለ፥ ወይም በበጉ ላይ የሆነ ችግር ካለ ይታያል። ለአራት ቀናት መቀመጥ አለበት።

74 አሁን አስተውሉ። እንዳንዶቻችሁ ምናልባት፡ በአስራአራተኛው ቀን መታረዱን አስባችሁ ይሆናል። ማለት፡ አስታውሱ፡ በጉን ከወሩ በአስረኛው ቀን ይወሰዱታል፡ ከወሩ በአስራ አራተኛው ቀን ይታረዳል፡ እያችሁ፡ ለአራት ቀናት ተጠብቋል።

75 አሁን፡ ኢየሱስ፡ በጉ፡ የእግዚአብሔር ስም፡ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ እስከ ሞቱ፡ ቀብሩ፡ እና ትንሳኤው በኋላ ድረስ ዳግመኛ አልወጣም። ለአራት ቀንና ለአራት ሌሊት በተቺዎች ተይዞ ቆየ። በጉ ለአራት ቀናት ተይዞ መቆየቱ፡ እንዴት ያለ ጥላ ነበር። ጲላጦስ የተናገረውም ያ ነበር፡ “በእርሱ ላይ ምንም ጥፋት አላገኘሁም።”

76 ሌላኛው ጥላ ደግሞ፡ ከሰውነቱ አንዲት አጥንት አለመሰበሯ ነበር፡ በጣም በሚደንቅ ሁኔታ፡ ሊሰብሩት አልቻሉም። መሰዋዕት በሚያርዱ ጊዜ፡ አጥንት አይሰብሩም ነበር። ከተሰበረ ግን፡ ተቀባይነት አልነበረውም። እናም “አስቀድሞ ሞቷል፡” ብለው በተናገሩ ጊዜ፡ የክርስቶስን እግሮች አጥንት ለመሰበር መዶሻውን ይዘው መጥተው ነበር። ጎኑንም ወጉት ከዚያም ደምና ውሃ ወጣ።

77 እዚህ ላይ ሌላ ታላቅ ነገር እንደገና አስተውሉ። በቀላሉ አላልፈውም፡ በዱቄቱ መሰዋዕት፡ በመሰዋዕቱ ላይ ደግሞ ተመስሏል።

አስታውሳለሁ በአንድ ወቅት፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ የነቢያት ትምህርት ቤት የሚባል ትምህርት ቤት ነበራቸው፡ እና የተለየ ትምህርት ቤት ነበር። እናም አንድ ቀን፡ ኤልያስ ወደዚያ ትምህርት ቤት እንደወጣ እናያለን። “እ… ” እነርሱም እንዲሄድላቸው ለመኑት፡ “አንተ እዚህ በመጣህ ቁጥር፡ የነገሮች ቁጥጥር ይበዛብናል፡” አሉት። በዚህም ምክንያት እንዲሄድላቸው ፈለጉት።

እነዚያም እራት ሊሰሩለት ወጡ። እና ብዙ ካህናት፡ ወይም ነብያት፡ እራት እንዲያዘጋጁለት፡ ጥቂት አተር ለማምጣት ወጡ። ሄደውም፡ ልብሰ ሙሉ ታላላቅ ነገሮች ሰበሰቡ፥ ተመልሰው በመጡ ጊዜ፡ እነሆ መርዛማ፡ የዱር ቅጠል ነበረ፡ እርሱንም ማሰሮው ውስጥ ጨመሩት። ማሰሮዎቹም ማብሰል በጀመሩ ጊዜ፡ እነሆ፡ አንድ ሰው፡ “ወዮ፡ ማሰሮው ውስጥ ሞት አለ። አሁንስ መብላት እንኳን አንችልም፡” አለ።

ኤልያስም “አንድ እፍኝ ዱቄት አምጡልኝ፡” አላቸው። ዱቄቱንም አንስቶ ወደ ማሰሮው ጨመረው፡ እና “ማሰሮው ተፈውሷል። አሁን ብሉ፡” አላቸው።

78 የዱቄቱ መሰዋዕት ክርስቶስ ነበረ። ለእህሉ ቁርባን የሚሆነውን፡ እህሉ አንድ አይነት ሆኖ መስለቅ አለበት፡ ዱቄቱም በተመሳሳይ መልኩ የተፈጨ መሆን አለበት። እርሱ ፈዋሽ መሆኑን ያሳያል። በሁለቱ ሕጎች፡ ይተካል፡ ሞትን አስወግዶ፡ ህይወትን ተካ። ሃሌ ሉያ! ሞት ባለበት፡ ሰፋራ፥ ክርስቶስ ሲገባ፡ ሕይወት መጣ። እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ ለዘላለምም ያው ነው። ሞትም ባለበት በዚያ፡ ሕይወት ሆነ፡ ምክንያቱም የዱቄቱ ቁርባን መሰዋዕት የሆነው፡ ክርስቶስ ገብቷልና።

79 እነዚህን ነገሮች ጊዜ አግኝተን አድቅቀን ለመለየት ብንሞክር ምንኛ ጥሩ ትምህርት ይሆን ነበር! አሁን አስተውሉ፡ ከጥላው ቃል አንዲት ቃል አልወደቀችም። ከጥላው፡ አንዲት ቃል አልወደቀም። እያንዳንዱ ምሳሌ በትክክል ተከናውነዋል።

በእግዚአብሔር የተመረጠ የአምልኮው ስፍራ እርሱ ነው፡ የእግዚአብሔር ስምም ለእርሱ ተሰጠ። የእግዚአብሔር የአምልኮው ስፍራ እርሱ ነው። የእግዚአብሔርም ስምም ለእርሱ ተሰጥቶታል። እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡ እርሱም የእግዚአብሔር ስም ነው። እርሱ የእግዚአብሔር ቃል እና የእግዚአብሔር ስም ነው። "ሥጋ የሆነው ቃል እርሱ ነው።" የእግዚአብሔር ቃል፡ የእግዚአብሔር በግ፡ የእግዚአብሔር ስም፡ እሱ አምላክም ነበር። ለእግዚአብሔር የተመረጠ እና ብቸኛው የአምልኮው ስፍራ፡ እንዲሁ ነበረ።

80 እግዚአብሔርም ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ ስፍራ አይቀበልም፡ ሌላ ስፍራ ላይ እሱን ማምለክ አትችሉም። "የሰውን ትእዛዛት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ፡ በከንቱ ያመልኩኛል፡" አለ። ዛሬ መንገዱ **ይህ** ነው መንገዱ **ያ** ነው እያሉ የሚያስተምሩ፡ የሃይማኖት መግለጫዎች፡ ዶግማዎች፡ እና ብዙ ነገሮች አሉ።

ኢየሱስም "መንገድና፡ እውነት፡ ሕይወትም እኔ ነኝ፡ በእኔ ካልሆነ በቀር ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ የሚችል ማንም የለም፡" ብሏል። በሌላ አነጋገር፡ "እኔ የበጎች በረት በር ነኝ። ውጭ ያሉት ሁሉ ሌቦች ናቸው።" ብቸኛው መቅረቢያው እርሱ ነው። በሩ እሱ ነው። መንገድ፡ እውነት፡ ሕይወት፡ በሙሉ እርሱ ነው፡ ብቸኛው መግቢያ፡ ብቸኛው ስፍራ፡ ብቸኛው አምልኮ፡ ብቸኛው ስም እሱ ነው።

ሁሉም ነገር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የተያያዘ ነው። ብሉይ ኪዳን ሁሉ ከእርሱ ጋር የተሳሰረ ነው። አዲስ ኪዳን ከእርሱ ጋር የተሳሰረ ነው። ቤተክርስቲያንም ዛሬ በትእዛዙ ቃል፡ ከእርሱ ጋር የተሳሰረች ናት። እግዚአብሔር ሰውን ለመገናኘት፡ ቃል የገባበት ሌላ ስፍራ፡ ወይም ሌላ ስም፡ ወይም ምንም ይሁን የለም፥ በተመረጠው የአምልኮው ስፍራ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

81 ልብ በሉ፡ እግዚአብሔር አምላኪዎቹን በዚህ አንድ ስፍራ ብቻ ለመገናኘት ቃል ገብቷል፡ ያም በራሱ ምርጫ ነው፥ በእኛ ምርጫ ሳይሆን፡ በአስተሳሰባችን ሳይሆን፡በአስተሳሰቡ፡ በምርጫው። ይህም ሰውንም ያስቀመጠበት፡ የመረጠበት ስፍራ ይሆናል። ስለዚህም ሰው የት እንደነበረ፡ በራሱ የመረጠውም ምርጫ እንደተረዳን፡ እንገነዘባለን።

82 እንግዲያውስ ሰው ያስቀመጠበት ስፍራ፡ እርሱም፡ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደሆነና፡ ከሱ በቀር ሌላ ስፍራ አለመኖሩን፡ ወይም ሌላ ስም አለመኖሩን በማወቃችን፡ በዚህ ረክታችኋልን? "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] አሁን፡ ዋናው ነገር፡ ስፍራው ያለበትን ቦታ ካገኘነው... የአምልኮ ስፍራው በክርስቶስ ዘንድ ብቻ ከሆነ በቀር፡ ሌላ ስፍራ የለም።

ንሰሃ ትገቡ ይሆናል፡ ሌላም ታደርጋላችሁ፡ አመለካችሁ ማለት አይደለም። ይቅርታ እየጠየቃችሁ ብቻ ነው። ጴጥሮስ እንዲህ አለ...

በበዓለ ሃምሳ ቀን፡ ሁሉም በልሳኖች ሲናገሩ፡ ታላቅ ምልክትና ድንቅ ሲደረግ ባዩ ጊዜ፡ መሳቅ ጀመሩ፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሳቀችባቸው፡ እንዲህም አለች፡- "እነዚህ ሰዎች አዲስ የወይን ጠጅ ጠግበዋል። እንደ ሰከረ ሰው ይሆናሉ። እ... " ድንግል ማርያም፡ እና መቶ ሀያዎቹ፡ ሁሉም፡ አንድ ላይ ነበሩ። በልሳኖችም እየተናገሩ፡ እንደ ሰከረ ሰው፡ ይንገዳገዱ ነበር። "እነዚህ ሰዎች አዲስ የወይን ጠጅ ጠግበዋል፡" አሏቸው።

83 ጴጥሮስ ግን፡ ተነሥቶ፡ እንዲህ አላቸው፡ “ወንድሞች ሆይ፡ እነዚህ ሰዎች በአዲስ የወይን ጠጅ የጠገቡ አይደሉም፡ ይህ ከቀኑ ሦስተኛው ሰዓት ነውና። ነገር ግን ይህ በነቢዩ ኢዩኤል የተነገረው ነው፡ ‘በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፡ ይላል እግዚአብሔር፡ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፥ በባሪያዎቼና በባሪያዬ ላይ ከመንፈሴ አፈስሳለሁ። በላይ በሰማይና በምድር፡ ምልክቶችን አደርጋለሁ፥ እሳት፡ የእሳት አምዶች፡ የጢስ ጭጋግ። ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት፡ እንዲህ ይሆናል፡ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።’”

84 ይህንም በሰሙ ጊዜ፡ ልባቸው ተነካ፡ እንዲህም አሉ፡ “ወንድሞች ሆይ፡ ምን እናድርግ?”

85 ጴጥሮስም፦ “ንስሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለኃጢአታችሁ ስርየት ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታም ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ለመጪው ትውልድ ሁሉ ነውና።” አሁን ይሄን ደርሰንበታል።

86 አሁን **ወደ** እሱ እንዴት እንደምንገባ መፈለግ አለብን። ወደዚህ የአምልኮ ስፍራ እንዴት እንገባለን? 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 12 ላይ፡ “በአንድ መንፈስ” በማለት፡ ያብራራልናል! በአንድ ቤተ ክርስቲያን አይደለም፡ በአንድ የሃይማኖት መግለጫ፡ በአንድ ፓስተር፡ በአንድ ጳጳስ፡ በአንድ ቄስ አይደለም። ነገር ግን፡ “በአንድ መንፈስ ቅዱስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡” እርሱም የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ነው፡ በዚያ አካል ውስጥ ሰላለው ስጦታ ሁሉ ተገዢ ነን። አዎን፡ ዎዳጄ! አባል መሆን፡ የእምነት መግለጫዎን መድገም፡ መውጣት፡ መውረድ፡ መጩባበጥ፡ ወይም ሌላ ምንም ነገር አይሰራም። ነገር ግን፡ በመወለድ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አካል እንጠመቃለን! ኣሜን። “በአንድ መንፈስ ቅዱስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።”

87 እና ያ አካል ምንድን ነው? “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃልም ሰጋ ሆነ በእኛም መካከል አደረ።” እንዴት በዚያ አካል ውስጥ ሆነን እንዴት የሱን ቃል እንክዳለን፡ ወይስ በአካል ውስጥ ባልሆነ በሌላ ሰፍራ እንዴት እናስቀምጠዋለን? ልናደርገው የሚገባን እንዴት ነው? እግዚአብሔር በመረጠው ሰፍራ!

88 ልብ በሉ፡ በሱ ዘንድ በትክክል ከተጠመቃችሁ፡ እርሱን ማመናችሁ ትክክለኛው ማረጋገጫ እርሱን ማመናችሁ ነው፡ ማለት ቃሉን።

የእርሱ አካል ነን እያላችሁ እንዴት ትክዱታላችሁ? እጄ የእኔ እጅ ስለመሆኑ እንዴት እክደዋለሁ? እንዲህ... እንዲህ ከካድኩት፡ የአእምሮ ችግር አለ ማለት ነው። እንዴት ይቻለኛል? እጄ የሚያስክደኝ፡ እግሬን የሚያስክደኝ፡ አእምሯዊ ችግር ካለብኝ፡ እግዚአብሔር የተናገረውንና የገባውን ቃል የሚክድ አማኝ ካለም የተሳሳተ መንፈሳዊ ችግር አለበት ማለት ነው። አማኝ-ተብዬው ላይ መንፈሳዊ ሰህተት አለ።

89 የአካሉ ብልት ስለሆናችሁ፡ ከቃሉ አንዲት መካድ አትችሉም። ከእርሱ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ ሰለ ተጠመቃችሁ የእርሱ አካል ናችሁ፥ በመንፈስ ቅዱስ፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አካል አመጣችሁ። እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው!

90 እግዚአብሔር የሚገናኝበት ስፍራ ነበረው—አብርሃምን በተገናኘው ጊዜ፡ አብርሃም በዚያ ስገደለት። በኪዳኑ ሁሉ ላይ!

የተሰፋው ቃልም በእናንተ ዘንድ፡ በእርሱ ይተረጎማል። ገብቷችኋል? በምትኖሩበት ዘመን ሊፈጽመው የገባው ቃል፥ በሰው ሁሉ የሚነበቡ፡ የተጻፈ የእግዚአብሔር መልእክት ትሆናላችሁ። እኛ እንዲህ ነን በምትሉት ሣይሆን፡ እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ በሚሰራው ነው፡ ይህም እኛ እንዲህ ነን ከምትሉት በላይ አብልጦ ይናገራል። እግዚአብሔር “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡” አለ። ይህ በአንተ በኩል ተናገረ።

91 አሁን ሊፈጸሙ ሰላላቸው ነገሮች፡ ስለዚህ ዘመን ተናግሯል። በዚህ ዘመን ያሉ አማኞች፡ ዛሬ የገባውን ቃል ማመን አለባቸው። እነርሱ ለመዳን፡ ወደ መርከብ ውስጥ መግባት እንደነበረባቸው፡ ለመዳን ከግብፅ እንደወጡ፥ ድኑ ዘንድ፡ በተመሳሳይ መልኩ ወደ ክርስቶስ፡ ወደ ቃሉ መልእክት መምጣት አለባቸው፡ እሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነውና።

92 ወደዚያ እንዴት ትገባላችሁ? በጥምቀት! በምን ጥምቀት፡ በውኃ ነውን? በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት! “በአንድ መንፈስ፡ ሁላችንም በዚህ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።”

93 የተሰጠ የተሰፋ ቃሉን፡ እ... እንድትተረጉሙት አይገባችሁም። እርሱ ራሱ በእናንተ ይተረጉመዋል፥ እርሱ በገባው የተሰፋ ቃል፡ እናንተ እያደረጋችሁ ባላችሁ ነገር ነው። እርሱን የምትከተለው ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እርሱን እንደምትመስል እስኪገነዘቡ ድረስ እጅጉን ትመስለዋለች።

ጴጥሮስና ዮሐንስ መልካም በሚባል ደጅ ላይ ስለ አንድ ሰው መፈወስ ሲጠየቁ አይታችኋል። እነዚያ ካህናት፡ “እንዲህ አስተውለናል፡” አሉ፡ “ሁለቱም መሃይሞች እና ያልተማሩ ሰዎች መሆናቸውን አስተውለዋል፡” ይሁን እንጂ ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ ተገንዝበዋል። ምክንያቱ፡ (ምን? ) እሱ ያደረጋቸውን ነገሮች ያደርጉ ሰለ ነበር ነው።

94 በአብ ስራ ላይ መዋል ነበረበት። ዛሬም ተመሳሳይ መሆን አለበት።

95 አሁን፡ ልብ በሉ፡ እሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው፥ እግዚአብሔርም፡ ብቸኛ በሆነው ስፍራ በእርሱ ዘንድ ይገናኛችኋል፥ ሰሙ ያኖርበት ዘንድ የመረጠው እርሱ ነውና፡ በኢየሱስ። “ኢየሱስ” የእግዚአብሔር ስም ነው። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ የሰሙ ማለት “የኢየሱስ ክርስቶስ” መጠሪያዎች መሆናቸውን፡ ልብ በሉ።

96 ማቴዎስ ሲናገር፡ “እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአብ፣ በወልድ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ሰም እያጠመቃችሁ አስተምሩአቸው።”

ሲላቸው፡ ዛሬ በተሳሳተ መንገድ ተርጉመውታል እንዲህ በማለት፡ “በአብ ስም፣ በወልድ ሰም፣ በመንፈስ ቅዱስ ሰም።” ይህ ፈጽሞ አልተጻፈም። ለአንድ እንደሚናገር፡ “በአብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡” “ስም፡” ይላል። **አብ** ስም አይደለም፡ **ወልድ** ሰም አይደለም፡ **መንፈስ ቅዱስ** ሰም አይደለም፥ መዓርግ ነው።

ከአሥር ቀን በኋላ፡ ጴጥሮስ መጣና እንዲህ አለ፡ “ንሰሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተጠመቁ።” ታዲያ አታድርግ

የተባለውን አደረግን? አድርግ የተባለውን አደረገ እንጂ። የአብ፡ የወልድ፡ እና የመንፈስ ቅዱስ ስም “ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ” ነውና። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠመቁ ሰዎች በሙሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።

97 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድም ሰው አልተጠመቀም። የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ በሮም፡ በኒቂያ ላይ እስኪደነገግ ድረስ ይህ ፈጽሞ አልነበረን። ከካቴኪዝም፡ የተገኘ፡ ተመሳሳይ ነገር የሚገልጥ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ ነው። ይኸው፡ በትክክል፡ **ፋክትስ ኦፍ አዎር ፌይዝ፡** እና የመሳሰሉት፡ ፍፁም የሮማ ካቶሊክ እምነት መግለጫዎች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሌለ ይነግሩአችኋል፥ ይሁን እንጂ በጳጳሱ ምክንያት፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፡ ቃሎቹን የመቀየር ስልጣን አለን ይላሉ። እኔ እቃወማለሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነውና። “ከዚህ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቃል የሚያጎድል ሁሉ፡” አለ ኢየሱስ፡ “ወይም በላዩ ላይ አንዲት የሚጨምር፡ ዕጣ ፈንታው ከህይወት መዝገብ ይጎድላል።” አንዲት ቃል፡ ዓረፍተ ነገር፡ ወይም አንቀጽ ሳይሆን፡ ቃል! “አንድ ቃል የሚያጎድል ማንም ቢኖር... ”

98 በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን በቃሉ አስታጠቀ። አንዲት ቃል፡ በተሳሳተ መንገድ በመረዳታቸው፡ ይህ ሞት ሁሉ፣ የልብ ህመም ሁሉ፣ ሐዘን ሁሉ መጣ። ሔዋን፡ ዓረፍተ ነገር አልተተላለፈችም፡ አንድ ቃል ብቻ ተላለፈች። ኢየሱስ በመጽሐፉ መኃል መጣ... ያ የመጽሐፉ የመጀመሪያው ነበርና።

ኢየሱስ በመጽሀፉ መኃል በመጣ ጊዜ፡ ምን አለ? “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፏል።”

በመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል፡ በራእይ ምዕራፍ 22 ላይ፡ 18ኛው ቁጥር፡ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ክፍል ላይ፡ ኢየሱስም ራሱን ተናገረ፡ እንዲህ ሲል፡ “ማንም ከዚህ መጽሐፍ አንድ ቃል ቢያጎድል ወይም በእርሱ ላይ አንዲት ቃል ቢጨምር እኔ እመሰክራለሁ፡ ዕድሉን ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ይጎድልበታል፡” ምክንያቱ ሐሰተኛ ነብይ ነው ህዝቡንም አስቷልና፡ ይህን በማድረጉ፡ ደማቸው ከእጁ ይፈለጋል።

99 አንዷ የአምልኮ ሰፍራ መጠበቅ አለብን፡ ያም፡ ቃል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ እርሱም ትላንትና፡ ዛሬም፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው። አሜን። በጣም ጥሩ። የምናመልክበት ሌላ ሰፍራ፡ አንድ እንኳ የለም፡ ይህን አስታውሱ። የመረጠውም እግዚአብሄር ነው።

100 ዮሐንስ፡ ያኔ ድሮ በአዲስ እና በብሉይ ኪዳን ማሰሪያ ላይ ነበረ። አሁን በደንብ ተከታተሉኝ። በደንብ ልብ በሉ። ዮሐንስ፡ ያ ታላቅ ንሰር፡ ታላላቅ ክንፎቹ ዘርግቶ፡ አንድ ቀን ከምድረ በዳ እየበረረ መጣ። በዮርዳኖስ ዳርቻ ላይ ተለኮሰ፡ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ድልድይ ያገናኘ ታላቅ ንሰር ነቢይ ነበር፡ ከግራ እና ከቀኝ ሁሉ አወጀ። አዋጁም ስለ ንሰሓ ቀን ነበር።

ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በመጡ ጊዜ፥ እንዲህ አላቸው፡ “ለራሳችሁ ‘አብራሃም አባት አለን፡’ ማለት አትጀምሩ፡’ እላችኋለሁ ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ያስነሣለት ዘንድ እግዚአብሔር ይችላልና።” ኦህ፡ ማይ!

ወንጌሉን እንዲህ መወርወር በጀመረ ጊዜ፡ እንዲህ አላቸው፡ “እነሆ እናንተ የማታውቁት፡ በመካከላችሁ የቆመ አንድ አለ። እኔም እስከ አሁን ድረስ አላወቅኩትም፡ እሱ ሲመጣ ግን አውቀዋለሁ። የጫማውን ክር ለመፍታት ብቁ አይደለሁም። እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል። መንሹም በእጁ ነው፥ አውድማውም ፈጽሞ ያጠራዋል፡ ገለባውም በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።”

101 ታላቁ የወንጌል ንስር፡ ከባባድ ውርጂቢኝ እያወረደባቸው በዚያ ነበረ። ያን ጊዜ እርኩሱ ብቅ አለ፡ ወይም በዚያ ዘመን ንጉስ የነበረው፡ ሄሮዶትስ፡ የወንድሙን ሚስት ማግባቱን፡ ታወጀ። እናንተስ ያ ታላቅ የወንጌል ንስር በዚያ ተገኝቶ ሳለ በነገሩ ላይ ዝም የሚል ይመስላችኋልን?

አንዳንዶቹ እንዲህ አሉት “ዮሐንስ ሆይ፡ ሄሮዶትስ እዛ ቁጭ ብሏልና፡ አደራህን ስለ ጋብቻ እና ስለ ፊቺ አሁን እንዳትሰብክ፡” አሉት።

102 ፊት ለፊቱ ሄዶ “አንተ እሷን ማግባት አትችልም ሕገ ወጥ ነውና፡” አለው። በትክክል!

እሱ፡ ምን፡ ነበር? ከምድረ በዳ የወጣ ንስር ነበር። እሱ በሰዎች ዛቻ እና ጉራ፡ በአንዳንድ የእምነት ተቋማት ውስጥ የሰለጠነ አልነበረም። እርሱ ግን በወቅቱ የሚመጣውን እንዲያውቅ፡ ከልዑል አምላክ ስልጣን ስር የተማረ ሰው ነበር። የመሲሑን መለያዎች ያውቅ ነበርና።

ሃሌ ሉያ! ቃሉ “እግዚአብሔር ይመስገን፡” ማለት ነው! አትፍሩ። ገና ማንንም አልጎዳሁም። ሞቅ አላለኝም። ያለሁበትን አውቃለሁ።

ኦህ፡ ሳሰበው፡ ያ ታላቅ በራሪው ንስር በዚያ ሳለ! “እርሱ ሲመጣ እኔ አውቀዋለሁ፡” ብሎ ተናገረ።

103 አንድ ቀን፡ እዚያ ቆሞ እየሰበከ ነበር። ካህናቱም ማዶ ላይ ነበሩ፡ እንዲህ አሉት፡ “ምን ማለትህ ነው የዘወትር መሰዋዕት የሚቋረጥበት ጊዜ ይመጣል፥ ይህ የገነባነው ታላቅ ቤተ መቅደስ፡ እና የሰራነው፡ ታላቁ የሐይማኖት ተቋም ይጠፋል?

እርሱም፡ “ይህ ሁሉ የሚጠፋበት ጊዜ ይመጣል” አላቸው።

“ሊሆን አይችልም። አንተ ሐሰተኛ ነብይ ነህ!”

104 ዞር ብሎ ተመለከተ። እንዲህም አለ፦ “እነሆ፡ ይህ ነው! እግዚአብሔር የመረጠው የአምልኮ ቦታ ይህ ነው። በጉ ይሄው ነው፡ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ እውነተኛው በግ አላቸው።” “እነሆ ሜቶዲስት፡ እነሆ ባፕቲስት፡ ወይም ካቶሊክ መጡላችሁ፡” አላለም። “እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ መጣ፡” አላቸው።

ብቸኛው የደህንነት ቀጠና በዚያ የእግዚአብሔር በግ ውስጥ ነው። መዳን በእርሱ ብቻ ነው፥ በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን፣ በየትኛውም እምነት መግለጫ፣ በየትኛውም ሕዝብ፣ በየትኛውም አባት፣ በየትኛውም እናት፣ የትኛውም ቅዱስ ሰው፡ ወይም በማንም፡ በቅዱስ ቦታ አይደለም። ለቤዛነት፡ እግዚአብሔር ስሙን ባኖረበት ሰው፡ በቅዱሱ አምላክ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ነው፡ እርሱ ስለ እኛ ስለ ሐጢአተኞች ዋጋ ከፈለ። መዳን ያለበት ስፍራ ያ ብቻ ነው። እኔ የቆምኩበት ዓለት እርሱ ነው።

105 ዮሐንስ ማንነቱን አወቀ። እንዲህ አለ፡ “እሱ ሲመጣ ሳየው አላወቅኩትም ነበር፡ ነገር ግን በዚያ በተማርኩበት ትምህርት ቤት... ” አባቱ በተማረበት ሰሚናሪ ማለቴ አይደለም፡ ካህን ለመሆን፡ አልሰለጠነም። ነገር ግን በነበረበት ምድረ በዳ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይጠባበቅ በነበረበት፡ ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ ሥነ መለኮታዊ ሴሚናሪ ውስጥ ነው፥ እግዚአብሔር ስለ እርሱ በተናገረው ነው እንጂ፡ አንዳንድ ሰዎች በፈለፈሉት አይደለም። ዮሐንስም አሻቅቦ ሲመለከት መንፈስ ሲመጣ አይቶ፡ እንዲህ አለ፦ “እነሆ እመሰክራለሁ፡ እርሱ ይህ ነው።” ኦህ፡ ማይ!

እነሆ የማምለኪያ ሰፍራችሁ ይህ ነው። መደበቂያችሁ ይህ ነው። የዓለምን ኃጢአት የሚያሰወግድ የእግዚአብሔር በግ ይህ ነው። የዓለምን ኃጢአት የሚያሰወግድ የእግዚአብሔር በግ እንጂ፡ ቤተ ክርሰቲያን፡ የሃይማኖት መግለጫ፡ ወይም ሌላ ምንም አይደለም።

106 ዮሐንስ እንዴት እንዳሰቀመጠው ተመልከቱ? “እናንተ ፈሪሳውያን፡ ሰዱቃውያን፡ ሄሮዳውያን ልክ ናችሁ፡” አላለም። “እነሆ በጉ፡” አላቸው። ሰፍራው ይህ ነው። ሰሙን የያዘው እርሱ ነው። እሱ ነው። ከሰማይ በታች ሌላ ሰም የለም!

107 ኢየሱስ ሰለ ዮሐንስ የተናገረውን አሁን ተመልከቱ። አንድ ቀን ዮሐንስ፡ የሚያደርገውን ለማየት ወደ እርሱ ላከ። ኢየሱስ ሰለ እርሱ እንዲህ አለ፡ “እሱ ታላቅ እና የሚያበራ ብርሃን ነበር፡” ከመምጣቱ በፊት፡ ከመጀመሪያው ምጽአቱ በፊት ያለውን መንገድ ያሳያቸው ዘንድ ሆነ። በደንብ ሰሙኝ። እንዳያመልጣችሁ። ኢየሱስ ሚልኪያስ 3 ላይ፡ “ዮሐንስ ያ ብርሃን ነበረ፡” ብሏል። ያለ ጥርጥር! የሚያበራው ታላቅ ብርሃን የነበረው ይህ ነብይ ብቸኛው መንገድ ኢየሱስ ማለት “በጉ፡” መሆኑን አስተዋውቋል። ካህናት የሚያወሩላቸው ሌሎች በጎች ሁሉና፡ ሌሎች ነገሮች ሁሉ፡ ሞኝነት ነበሩ። ይኸው “በጉ!” ታላቅ የሚያበራ ብርሃን ያለው ሰው፡ ኢየሱስም እንዲሁ ነኝ ብሏልና።

ሚልክያስ 3 ላይ፡ “እነሆ መልእክተኛዬን እልካለሁ መንገድንም በፊቴ ያሰተካክላል” አለ። መንገዱን እንዲያዘጋጅ የተላከው ሰውም፡ ሰፍራው ይህ ነው፡ በማለት አሰታወቀ። “እሱ ነው! አለ ጥርጥር። እሱ ነው! የተከተለውን ምልክት አይቻለሁ። እርሱ እንደሆነ አውቃለሁ፥ ከሰማይ የወረደው ብርሃን በእርሱ ላይ ሲያርፍ አየሁት።” እሱ እንደሆነ፡ እርግጠኛ ነበር።

108 እንግዲያውስ፡ ወንድሜ ሆይ፡ በመዝጊያ ላይ፡ ይሄን ልጠይቅህ። እስኪ ይህን እንበል። በሚልክያስ 4 ላይስ፡ እኛ ደግሞ ሌላ ንሰር እንዲመጣልን ቃል አልገባምን፡ እርሱን የእሳት አምድ እንደሚከተለው፡ የሳተችውን ቤተ ክርሰቲያንን ዕብራውያን 13፡8 እርሱ እንደሆነ፡ “ትላንትናም፡ ዛሬም፡ እሰከ ለዘላለም ድረሰ ያው” መሆኑን? ከበረሃ እየከነፈ የሚመጣ ሌላ እንዳለ ቃል አልተገባልንምን? አሜን! በትክክል እውነት ነው። ይህም የሰው ልጅ ወይም (ንሰሩ) ራሱን ከሚገልጥበት ከሉቃስ 17፡30 ጋር፡ እጅግ አንድ እና ተመሳሳይ ነገር ነው እሱም የሐይማኖት ተቋማት፡ እና የመሳሰሉ የአምልኮ ሰፍራዎች ከንቱ ለማድረግ ነው!

እግዚአብሔር ሰፍራውን መረጠ። ዮሐንስም “እነሆ ይህ ነው፡” አለ!

109 በዚህ ዘመንም ሚልክያስ 4 ላይ፡ “የልጆቹን ልብ ለመመለስ፡” ተመሳሳይ ነገር ቃል ተገብቶልናል፡ እርሱ አልሞተም ለማለት፡ ጥምቀት በኢየሱስ ስም ስለመሆኑ፡ ሰሙ ለድሮ ዘመን አለመሆኑ፡ ነገር ግን ዛሬም ያው ስለመሆኑ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለአሁኑ ዘመን ናቸው። አሜን። ሌሎች የአምልኮ ሰፍራዎች ሁሉ ከንቱ ለማድረግ፡ የኋለኛው-ዘመን ንስር ሰራው ያ ነው፡ ሌላው ነገር ሁሉ ከንቱ ሞኝነት መሆኑን ለማሳየት፡ የሐይማኖት ተቋም የማይረባ ስለመሆኑ፡ እርሱ ትላንትናም፡ ዛሬም እስከ ዘለአለም ድረስ ያው መሆኑን፡ እንደገና በተመሳሳይ ምልክቶች ያሳያቸው ዘንድ ነው። ሃሌሉያ!

110 በተጨማሪም፡ በራዕይ 4:7 ላይ፡ ያየናቸው አራት እንስሶች ነበሩ።

እንዳየነውም፡ የመጀመሪያው... አንበሳ፡ መሆኑን አይተናል። የዚያን ዘመን ተግዳሮት ለመመከት የወጣው እንስሳ፡ የይሁዳ ነገድ አንበሳ ነው።

ከእርሱ በኋላ ቀጣዩ እንስሳ መጣ። የሚቀጥለው እንስሳ፡ በሬ መሆኑን አየተናል፡ እርሱም የሸክምና፡ የመስዋዕት እንስሳ ነው። በሮማ ካቴድራል ዘመን፡ ቤተክርስቲያን ሞተች፥ መስዋዕት።

ቀጥሎ የመጣው፡ ሰው ነበረ፡ የሰው ፊት የነበረው እንስሳ ነበር። ያም ሰው የተሐድሶ አራማጆች ነበሩ፡ የሰው ትምህርት፡ ቲኦሎጂ፡ እና የመሳሰሉ ነበሩ።

ነገር ግን በመጨረሻ የሚበር እንስሳ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደተናገረው፡ በስተመጨረሻ የሚመጣው እንስሳ የሚበርር ንስር ይለዋል። ሃሌ ሉያ! ነብዩም ደግሞ እንደተናገረው፡ በዚህ ዘመን፡ “ብርሃን ይሆናል።” ኦህ፡ ማይ! “በዚያ ዘመን ብርሃን ይሆናል።”

111 የተሐድሶ አራማጆች ቀን ነበረ። ጥላ ብቻ የሆነ ዘመን አለ፡ ቀንም ማታም የማትሉት ዘመን። ሲመሽ ግን፡ በንስሩ ዘመን ግን፥

በንስሩ ዘመን ብርሃን ይሆናል፡
የክብር መንገድ በእውነት ይገኛል፥
የዘመኑ ብርሃን ሆኗል በውሃው ስር፡
በድንቅ ሰሙ በኢየሱስ በመቀበር።
ወጣት ሽማግሌ፡ ሁሉም ንስሃ ይግባ፡
መንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ያስገባችኋልና፥
የምሽቱ ብርሃኖች መጥተዋል፡
እግዚአብሔር እና ክርስቶስ አንድ መሆኑ ተረጋግጧል።

112 አሜን! ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡ የእግዚአብሄር ብቸኛ የተመረጠ የአምልኮው ሰፍራ። ኦህ፡ ይህ መልእክት ወደ ማን መጣ፡ ወደፊትስ ምን ያደርጋል? በሱ ዘመን ላይ ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡ ሌላውስ (ምንድነው?) ልጆቹን ወደ ቤታቸው ወደ እውነተኛው ተሰፋይቱ ምድር ይቀበላቸዋል፡ የእስራኤልን ልጆች በምድረ በዳ በመራቸው በተመሳሳይ የእሳት ዓምድ ምልክት ይመራቸዋል።

እግዚአብሔር የመረጠው የአምልኮ ሰፍራ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ብቸኛው ሰፍራ እርሱ ነው። እግዚአብሔር የሚያድንበት ብቸኛው ስም ይህ ነው። በሰማይ ውስጥ ያለውን ቤተሰብ የሰየመበት ስም ይህ ነው፡ በምድር ላይ ሳለም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይባላል።

113 ቤተ ክርስቲያን ሆይ፡ ሰዎች ሆይ፡ ኃጢአተኞች ወዳጆቼ ሆይ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አትታመኑ። በማንኛውም ሰባኪ ትታመኑ። ያድናችሁ ዘንድ በማንም ሰው አትታመኑ። በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን፡ በየትኛውም የሐይማኖት መግለጫ፡ በየትኛውም የሐይማኖት ተቋም አትመኑ። የዘመኑ ብርሃን እርሱ ነውና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ታመኑ።

አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡
የክብር መንገድ በእውነት ይገኛል፡
የዘመኑ ብርሃን ሆኗል በውሃው ስር፡
በድንቅ ስሙ በኢየሱስ በመቀበር።
ወጣት ሽማግሌ፡ ሁሉም ንስሃ ይግባ፡
መንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ያስገባችኋልና፥
የምሽቱ ብርሃኖች መጥተዋል፡
እግዚአብሔር እና ክርስቶስ አንድ መሆኑ ተረጋግጧል።

114 ኦህ፡ ወንድሜ፡ እህቴ ሆይ፡ ገና ንስሓ ካልገባችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ካልተጠመቃችሁ፡ ዛሬ ማታ ይህን ለመፈጸም ትወዳላችሁን? እርሱን ወደምታመልኩበት ስፍራ ያደርሳችሁ ዘንድ ለእግዚአብሄር ዕድል ትሰጡታላችሁን? ልብ በሉ፡ ከዚያ ውጪ፡ አምልኮአችሁን እንደሚቀበላችሁ እና እንደሚያገኛችሁ እግዚአብሔር ቃል የገባላችሁ ስፍራ የለም።

115 እንዲህ ትሉኛ ይሆናል፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እኔ የማመልከው ከልቤ ነው!” ቃየንም እንዲሁ ነበር። አቤል ያደረገውን ማንኛውንም ዓይነት መሥዋዕት አድርጓል፡ ይሁን እንጂ መስዋዕቱ የተሳሳተ መሥዋዕት ነበር። ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ፡ አስራት ልታወጡ ትችላላችሁ፡ እንደማንኛውም ወንድ እና ሴት፡ የክርስቲያን ግዴታችን ልትወጡ ትችላላችሁ።

አሁን ላለፉት ሰላሳ ዓመታት፡ እዚህ ከተማ ዙሪያ፡ ይህንኑ መልእክት እያወጅኩ ቆይቻለሁ። አርጅቻለሁ። ከእንግዲህ አብሬአችሁ ብዙ አልኖርም። ነገር ግን ይህን አስታውሱ፡ ድምፄ ተቀድቷልና፡ በፍርድ ቀን፡ እናንተን ይቃወማችኋል።

116 እግዚአብሔር ስሙን ያስቀመጠው አንድ ቦታ ብቻ ነው፡ ያም በቤተክርስቲያን ውስጥ ሳይሆን፡ በኢየሱስ ውስጥ ነው። አንድ የአምልኮ ስፍራ ብቻ አለ፡ ተቀባይነት የምታገኙበት ስፍራ አንድ ብቻ አለ፡ እርሱም በተወደደው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ነው። “ይድኑበት ዘንድ፡ ከሰማይ በታች ለሰዎች የተሰጠ ስም፡ ሌላ የለምና፡” ቤተ ክርስቲያን አይደለም፡ የሃይማኖት መግለጫ አይደለም፡ ሌላ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ!

የዘመኑ መልእክት ማለትም ይህ ነው፡ “የልጆቹን ልብ፡ አንድ ጊዜ ለቅዱሳን ወደ ተሰጠ እምነት ለመመለስ።” ዛሬ ማታ አትቀበሉትም ወይ?

አንገታችንን ደፍተን ሳለም።

117 በጸሎት መታወስ የምትፈልጉ፡ እጆቻችሁን ብቻ ታነሳላችሁ። የመሠዊያ ላይ ጥሪ ማድረግ አንችልም፡ በጣም ብዙ ናቸው። እግዚአብሀር ይባርክህ። ማይ! በግራዬ በኩል፡ በግምት ሶስት መቶ ያህል ይሆናሉ።

118 እስኪ በቀኝ ያላችሁስ፡ እጆቻችሁን ከፍ እያደረጋችሁ፡ "መታወስ እፈልጋለሁ፡" ብትሉስ። በቀኝ በኩል፡ በግምት መቶ ሃምሳ፡ ወይም ከዚያ በላይ ይሆናሉ።

አንድ ባለ ትልቅ የውኃ ገንዳ ተበርናክል አለን፡ እንዲሁም የተወደደ ፓስተር፡ ፓስተራችን፡ ወንድም ኦርማን ኔቪል፡ ረዳቶች፡ እዚህ የምታገኟቸው ሰዎች ሁሉ አሉ። በየቀኑ፡ በየምሽቱ፡ በየሰዓቱ፡ ለመጠመቅ የሚፈልጉ፡ ንስሓ የሚገቡ ሰዎች፡ ሁልጊዜም ይጠብቃሉ። ትእዛዙን የምትታዘዙ ከሆነ፡ በርግጥም፡ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ለመቀበል በልባችሁ ቅኖች ናችሁ።

119 አንድ ብቻ አምልኮ ሰፍራ አለና። እንግዲህ፡ ተበርናክሉ ውስጥ አይደለም። በክርስቶስ ውስጥ ነው። ወደ እሱ እንዴት እንገባለን? "በአንድ መንፈስ ሁላችንም ወደዚህ አንድ አካል በመጠመቅ።"

እንጸልይ።

120 አምላኬ ሆይ፡ እነዚህ እጆች ወደ ላይ ሲነሡ፡ ከዚያ እጅ በታች በልባቸው ያለውን ያሳያል፡ ይህም ከአንተ እርዳታ መፈለጋቸው እርግጠኛ መሆናቸውን የሚገልጽ እምነት ነው። አባት ሆይ፡ ለእያንዳንዳቸው እጸልያለሁ። ቃልህም እጠቅሳለሁ። እንዳልከውም፡- "ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ወደ ፍርድም አይመጣም፥ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ።"

አባት ሆይ፡ ለጥቂት ሳምንታት ከከተማ ወጥቼ፡ ሰመለስ፡ "እከሌ**ስ**? " ብዬ ስጠይቃቸው?

"እንዴ፡ እሱ'ማ ሞተ።"

"እሺ፡ እንትናስ... "

"እሱም ሞቷል።"

121 አምላኬ ሆይ፡ አንድ በአንድ ሁላችንም እንጠራለን፡ በሞት ጥላ ሸለቆ መካከል ለመራመድ ፈተናውን አንድ በአንድ መጋፈጣችን አይቀርም። ይህም ደግሞ እያንዳንዳችን፡ ሟቾች በመሆናችን ነው። ዛሬ ማታ፡ ግን፡ እኛ በእርሱ ብናምን፡ በስሙም ብንጠመቅ፡ ወደ ውስጥ እንደምታስገባን፡ ተማጽኖህን አቅርበህልናል። በዚህ አካል ውስጥም፡ የክርስቶስ አካል፡ ማለት በቤተክርስቲያን ውስጥ ሳይሆን፡ በክርስቶስ አካል ውስጥ፡ አካሉ ቀድሞ የተፈረደበት አካል ነው። ወደ ፊት ፍርድ ፊት አይቀርብም። እግዚአብሔር በዚያ አካል ላይ ቁጣውን አፈሰሰ፡ ስለዚህ ያ አካል ከሐጢአት ነጻ ነው፥ ስለዚህ፡ በእርሱ ዘንድ መሆናችን፡ እሱ ለእኛ ማስተሰርያ ሆኖ ስለሞተልን፡ ከሐጢአት ነጻ ያደርገናል። በዚያም እርስ በርሳችን ኅብረት አለን፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም፡ ከኃጢአትና ከርኵሰት ሁሉ ንጹሕ ያደርገናልና።

122 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ እያንዳንዳቸውን ወደ መንግሥትህ እንድታፈልሳቸው እጸልያለሁ። ይሁን፡ አምላክ ሆይ። አንዳቸውም አይጥፉ፥ ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ፡ አዋቂ ወንድ ወይም አዋቂ ሴት አይጥፉ። ጌታ ሆይ፡ አንዳንድ የራሴ ሰዎች እዚህ ምሽት ላይ፡ ከደሙ ስር ያልሆኑ፡ ዘመዶቼ አሉ። አቤቱ የአባቴ ቃሎቼ ምንኛ አስታውሳቸዋለሁ! አሁንም አምላክ ሆይ፡

እንዳቸውም እንዳይጠፉ፡ እጸልያለሁ። ይሁን በለን፡ ጌታ ሆይ። ማመን ባሉብኝ አቅም ሁሉ፡ አቤቱ አሁን አንተን አምናለሁ።

123 ዛሬ ማታ እዚህ ቦታ ባሉት ወንድሞቼ፡ እህቶቼ፡ ወዳጆቼ ላይ፡ እንዲሁም በሰልክ መሰመር ባሉት ሁሉ ላይ ውረድ። ከምሰራቅ የባህር ዳርቻ እሰከ ምዕራብ ድረስ፡ በልዩ ልዩ ግዛቶችን ውሰጥ ያሉ እያደመጡ ይገኛሉና። አምላክ ሆይ፡ እዚያ በቱክሰን ምድረበዳ፡ በካሊፎርኒያ፡ በኔቫዳ፡ እና በኢዳሆ በረሃዎች፡ በምሰራቅ ማዶ እና በዙርያ፡ በቴክሳሰ ሰላሉ ሁሉ፥ ይህ ግብዣ ሲቀርብላቸው፡ በትናንሽ አብያተ ክርሰቲያናት፡ በማድያዎች፡ በቤቶች ውሰጥ—ተቀምጠው በማዳመጥ ላይ ሰላሉ ሰዎች፡ እጸልያለሁ። አምላክ ሆይ፡ ያ የጠፋው ወንድ ልጅ ወይም ሴቷ ልጅ፡ ወንድ እና ሴት ሁሉ፡ በዚህ ሰዓት፡ ወደ አንተ ይመለሱ። አቤቱ አሁን ይሁን በለን። ጊዜ ሳለ ይህን የደህንነት ቦታ እንዲያገኙት፡ በኢየሱሰ ሰም እንጠይቃለን።

የግድግዳው ጽሕፈት፡ የመሬት ግራ መጋባት፡ ሰናየው፡ ነጻ ለመውጣት ጊዜው አሁን እንደሆነ እንገነዘባለን። ኢየሱሰ በገባው ቃል መሠረት፡ ከፊሉ የአገራችን ምድር፡ በመሬት መንቀጥቀጥ እየሰጠመ ይገኛል። እጅግ አይርዘምባቸው፡ ጌታ ሆይ። የጉባኤው፡ የወንጌሉ ትሩፋቶች አድርገን በፊትህ እናቀርባቸዋለንና፡ አሁን በኢየሱሰ ሰም፡ ይቀበሉት። አሜን።

124 ታምኑታላችሁ? እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እሰኪ በግራዬ ያላችሁ፡ ይህ እውነት መሆኑ ሰንቶች ታምናላችሁ? እጃችሁ ይነሣ። በቀኜሰ ሰንቶች ናችሁ? እጃችሁ ይነሣ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ማየት የቻልኩትን፡ ሁላችሁ። ወዳጆች ሆይ፡ እውነት ነው። እውነት መሆኑን እግዚአብሔር ያውቃል።

125 እርሱ ሆናችሁ፡ በውሰጡ እሰከሆናች ድረሰ፡ እርሱ ለሞተለት ነገር ሁሉ ባለ ድርሻ ናችሁ። እርሱ የሞተው ለምንድን ነበር? “እርሱ ሰለ መተላለፋችን ቆሰለ፡ ሰለ በደላችንም ደቀቀ፥ የደህንነታችን ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፡ በእርሱም ቍሰል እኛ ተፈወሰን።” ይህን ታምናላችሁ? አሁን ሰለ መፈወሰ ሰርየቱ ታማናላችሁን?

126 በመካከላችን የታመመ አለ? በቀኛም ሆነ በግራ ያላችሁ፡ እጃችሁን አንሡ። በጣም ብዙ ታማሚ አለ። ሰልፍ መጥራት አልችልም። አያችሁ፡ አልችልም... መድረኩ ላይ መውጣት አልችልም። ምንም አይነት ማድረጊያ መንገድ የለውም።

በሌሎች ቦታዎች፡ ለታማሚዎች የጸሎት ጉባኤ እያደረጉ ነው፡ በቸርቾቹ ላይ፡ እና በተበርናክል እየተደረገ ይገኛል።

አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። ሰንት አማኞች አላችሁ? እጃችሁን አንሡ። በጣም ጥሩ። ቃሉን እጠቅሰላችኋለሁ፡ እርሱም ክርሰቶሰ ነው። የኢየሱሰ የመጨረሻ ተልእኮ ለዓለም፡ ማለቴ፡ ለቤተክርሰቲያን፡ እንዲህ አለ፡ “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፥ እጃቸውን በድውዮች ላይ ቢጭኑ፡ ይድናሉ።” እውነት መሆኑን ሰንቶች ታውቃላችሁ፡ ማርቆሰ 16 ላይ፡ ይናገራል፡ “ኣሜን።” [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።—አርታዒ።] በጣም ጥሩ። እንደ አማኞች እንዲህ እጠይቃችኋለሁ በፊታችሁ ባለው ሰው ላይ እጃችሁን ጫኑ። እጆቻችሁን ከፊት ለፊታችሁ ባለው ሰው ላይ ጫኑበት፡ እና እያንዳንዳችን አሁን

አንዳችን ለሌላው ጸሎት እንጸልይ። እጃችሁ አጠገባችሁ ባለው አንድ ሰው ላይ ጫኑት።

127 ጌታ ሆይ፡ እዚህ በፊቴ ላይ የመሃረብ ሳጥን፡ ትናንሽ የተቆራረጡ ነገሮች አሉ፡ አንድ ቦታ ላይ ተኝታ፡ እየሞተች ላለች አሮጊት፡ ሞት አፋፍ ላይ ላለ ህጻን፡ በየስፍራው ላሉ ህሙማን ሁሉ። ከጳውሎስ አካል መሃረብና ጨርቅ ወስደው በሽተኞች ላይ ያደርጉባቸው እንደነበረ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንብበናል፥ ክፋ መናፍስት፡ ርኩሳን መናፍስት፡ ደዌ፡ እና ህመም፡ ከሰዎች ይሸሽ ነበር። አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ እኛ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳልሆንን እናውቃለን፡ ይሁን እንጂ አንተ አሁንም እግዚአብሔር-ያዘጋጀው ብቸኛው የአምልኮ ስፍራ፡ ኢየሱስ መሆንህን እናውቃለን። አሁንም፡ ዛሬ፡ እነዚህ ሰዎች ልክ እንደ ድሮዎቹ ሰዎች፡ ተመሳሳይ እምነት ማመናቸው መስክረዋል። አንተም በእውነት መንገድ አበጀህላቸው! እኔም እጆቼ በእነዚህ መሃረቦች አድርጌ ደዌ እና በሽታው ከህዝቡ ከሰውነታቸው እንዲለቅ ይህ ነገር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የነካው ሰው ህመሙ እንዲለቀው አዛለሁ።

128 አሁን፡ እስራኤል ከግብፅ ሲወጡ፡ በድርሻቸው ጉዞ ላይ፡ እንደነበሩ እናውቃለን፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር በመንገድ ላይ ነበሩ። መንገዳቸው ላይም ቀይ ባህር ተጋፈጣቸው። እግዚአብሔርም በእሳት ዓምድ ውስጥ ሆኖ አየ፥ ባሕሩም ፈራ፡ ወደ ኋላውም ተንከባለለ፡ እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲያልፍም ፈቀደ። አምላክ ሆይ፡ ዛሬም፡ በኢየሱስ ደም አልፈህ ተመልከት፡ ህመም ይንከባለል፡ ሰይጣንም ይገሰጽ። ህዝቡም ወደ ተስፋይቱ ጤና እና ብርታት ይሻገሩ፡ እግዚአብሔር እንዳለው፡ "ከሁሉም በላይ፡ በጤንነትዎ እንዲበረቱ እመኛለሁ።"

129 አሁንም ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ የእነዚህ ሰዎች እጅ፡ አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ሲጭኑ አይተሃል፡ ይህም አንተ "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡" እንዳልህ፡ የእምነታቸው ማሳያ ነው። በራሳቸው መንገድ፡ እርስ በርሳቸው እየጸለዩ ነውና። አጠገባቸው ያለውን ሰው እየጸለየላቸው ነውና።

130 አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ይህ ተግዳሮት ተጋፍጦናል፡ ይህም ሰይጣን፡ ትልቁ ግርዶሽ፡ የእግዚአብሔርን ልጅ የመያዝ መብት የለውም። የተሸነፈ ፍጡር ነው። ብቸኛው የአምልኮ ስፍራ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ብቸኛውና እውነተኛው ስም፡ በቀራንዮ አሸንፎታል። ደዌን ሁሉ፡ በሽታን ሁሉ ድል በማድረጉ፡ አሁን ደሙን እንጠራለን።

ሰይጣንም ይህን ጉባኤ ለቆ እንዲሄድ አዘዋለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከዚህ ሕዝብ ውጣ፡ ነጻም ይሁኑ።

131 በተጻፈው ቃል መሠረት ፈውሳችሁ የተቀበላችሁ ሁላችሁ፡ በእግራችሁ በመቆም እንዲህ ብላችሁ መስክሩ፡ "አሁን ፈውሴን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተቀብያለሁ በሉ።" በእግሮቻችሁ ቁሙ።

እግዚአብሔር ይመስገን! ይኸው። የአካል ጉዳተኞች እና ሌሎች እየተነሱ ነው፡ ወደዚህ ተመልከቱ። እግዚአብሔር ይመስገን! በቃ። እመኑ ብቻ። እሱ እዚህ ነው። እንዴት ድንቅ ነው!

132 ከጉባኤው ውጪ፡ በመስመር፡ ከውጪ ያላችሁ፡ ይህን ማየት በቻላችሁ! እስከገባኝ ድረስ፡ ሁሊኡም ሰው በሚባል ደረጃ፡ አብዛኛዎቹ፡ በዚህ ሰዓት

ቆመዋል። ኦህ፡ እንዴት ያለ ድንቅ ጊዜ ነው! የጌታ መገኘት፡ ያ ነው! "የጌታ መገኘት ባለበት በዚያ፡ አርነት አለ፡ በዚያ ነጻነት አለ።" የእግዚአብሔር መንፈስ ነፃ ያደርገናል።

133 አሁን እርሱ ፈውሶናል፡ እናምነዋለን። አድኖናልና፡ እናምነዋለን። መጠመቅ የምትፈልጉ፡ ገንዳው ተዘጋጅቷል። በማንኛውም ጊዜ፡ በማንኛውም ሰዓት መምጣት በፈለጋችሁ ሰዓት፡ ተዘጋጅቶ የሚጠብቅ ሰው በዚያ አለ።

አሁን እደሚመስለኝ፡ ከመዘጋታችን በፊት፡ የቀድሞ የቤተ ክርስቲያን መዝሙር መዘመር አለብን። "እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ ቀድሞ ስለወደደኝ።" እጆቻችንን ወደ እግዚአብሔር አንስተን በሙሉ ልባችን እንዘምረው!

ጠዋት ዘጠኝ-ተኩል ላይ፡ እዚህ ህንጻ ላይ፡ ልናገኛችሁ እንፈልጋለን፡ **ጋብቻ እና ፍቺ** በሚል ርዕስ እንገናኛለን። በጣም ጥሩ።

አሁን አብረን እንዘምር።

እወደዋለሁ፡

ይህ ታላቅ ጉባኤ አሁን ይዘምረው! ከውጭም፡ በመሰመር ላይ ያላችሁ ሁላችሁ፡ እናንተም ዘምሩት።

ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

134 የተደረገው የት ነበር? በቀራንዮ ዛፍ ላይ። እንደገና እየዘመርን ሳለ፡ አጠገባችሁ ካለው ሰው ጋር ሰላምታ እየተለዋወጣችሁ፡ "መጸተኛ ሆይ፡ እግዚአብሔር ይባርክህ፡" ተባባሉ።

እ... (... ? ... )
ቀድሞ ስለ...
መዳኔንም ገዛሁ
በ...

135 እህ፡ አትወዱትም ወይ? እሱ አይደንቅም ወይ? እሱ የመደበቂያ ስፍራችሁ ነውን? በምታደክም ምድር ዓለት ነው፡ በማዕበል መካከልም ጥላ ነው፡ እኔ የማውቀው ብቸኛ መጠለያ እርሱ ነው። ስለዚህ፡-

እምነቴ አንተን ይላል፡
የቀራንዮ በግ ሆይ፡
መለኮታዊ አዳኝ፥
አሁን ስጸልይ ስማኝ፡
ኩነኔ አሁን አንሳልኝ፡
ከዚህ ቀን በኋላ
የአንተው ሰው አርገኝ!

እጆቻችን ከፍ አድርገን እንዘምረው።

እምነቴ አንተን ይላል፡
የቀራንዮ በግ ሆይ፡
መለኮታዊ አዳኝ፥

አሁን ሰጸልይ ሰማኝ፡
ኲነኔ አሁን አነሳልኝ፡
ከዚህ ቀን በኋላ
የአንተው ሰው አርገኝ!

አንገታችንን ዝቅ እንዳለ በዜማ እንዘምረው።

በህይወት ድንግዝግዝ ሰዓዝ፡
ኃዘን በዙርያዬ ሲሰራጭ፡
አንተኑ መሪ ሁነኝ፥
ጨለማው ብርሃን አርግልኝ፡
የሀዘንን እንባ አብሰህ፡
እንዳልሰትም ጠብቀኝ
ከጎንህ እንዳልርቅ።

አንገታችሁ እንደደፋችሁ፡ ተወዳጁ ፓስተራችን፡ ወንድም ኦርማን ኔቪል፡ ጉባኤውን ያሰናብትልናል።

65-0220 በእግዚአብሔር የተመረጠ የማምለኪያ ስፍራ
ፓርክቪው ጁኒየር ሀይ ስኩል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org